# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 226 ሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## «ኢትዮጵያ ከነበረችበት የጦርነት ጨለማ ብርሃን ወደ ሆነው ሰላም ተሸጋግራለች»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

ጌትነት ምህረቴ




አዲስ አበባ፡- ጦርነት ጨለማ ነው፤ ሰላም ብርሃን ነው፤ ኢትዮጵያ ከነበረችበት የጦርነት ጨለማ ብርሃን ወደ ሆነው ሰላም ተሸጋግራለች ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ። ጦርነት ይብቃ ሰላምን እናጽና በሚል የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በሂደቱ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሁሉ የእውቅና እና ምስጋና መርሃ ግብር ትናንት በአዲስ አበባ ወዳጅነት አደባባይ ተካሂዷል።

በመርሐግብሩ ላይ መልዕክት ያስተላለፉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች ለልማቷ ለአንድነቷና ለሰላሟ አብዝታ ትሠራለች፤ ጦርነት ጨለማና ክፉ ነው፤ ከአፍና ከአፈሙዝ የሚወጣው ውስጥና ስጋን የሚገድል ነው፤ ሰላም ብርሃን ነው። አሁን ኢትዮጵያ ከነበረችበት የጦርነት ጨለማ ወደ ብርሃን ወደ ሆነው ሰላም ተሸጋግራለች ብለዋል።

ጠብን አቁሞ ሰላምን ለመፍጠር በቂ ያልሆነ ምክንያትና ትክክለኛ ያልሆነ ጊዜ የለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሰላም ያለማል ያበለጽጋል፤ በቀለለ መንገድ ወጥቶ መግባት እንዲቻል ያደርጋል። ስለሆነም ይህን ሰላም አጽንቶ መቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል።

«ኢትዮጵያ ከነበረችበት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የኢትዮጵያ ግዙፍ ኢኮኖሚ ምስጢሮች

አዲሱ ገረመው

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይ.ኤም.ኤፍ) በቅርቡ በከለሰው የ2023 የኢኮኖሚ ትንበያ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገራት ኢትዮጵያ ሦስተኛው ግዙፍ ኢኮኖሚ እንደሚኖራት አስታውቋል። አገሪቷም በአሁኑ ወቅት ከአፍሪካ አምስት ጠንካራ ኢኮኖሚ ባለቤት አገራት መካከል አንዷ ሆናለች። ይህ የአገሪቷን መዳረሻ ምን ላይ ሊያስቀምጥ ይችል ይሆን?

የኢትዮጵያ ግዙፍ ኢኮኖሚ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ዳኘው አይጠገብ

### በትግራይ ክልል በተያዘው ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ ይጀመራል

ገጽ 4

## የአፍሪካ አገራት በኢትዮጵያ አጋጥሞ የነበረው ችግር ከተፈታበት መንገድ ትምህርት ሊወስዱ ይገባል ተባለ

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- በግጭት ውስጥ ያሉ የአፍሪካ አገራት በሰሜን ኢትዮጵያ አጋጥሞ የነበረው ችግር ከተፈታበት መንገድ ትምህርት ሊወስዱ እንደሚገባ ተገለጸ።

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በመንግሥትና ሕወሓት የሰላም ስምምነት የመጣውን ውጤት ተከትሎ «ጦርነት ይብቃ ሰላምን እናጽና» በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ወዳጅነት ፓርክ የእውቅና እና ምስጋና መርሃ ግብር ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ ንግግር ያደረጉት የቀድሞው የኬንያ

የአፍሪካ አገራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬኒያታ





















ሰላማዊት ዳዊት

# የገበታ ፕሮጀክቶች

## የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ በማራዘም ገቢን እያሳደጉ ነው

**ዳግማዊት አበበና ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለአገር እና ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች ቱሪስቶች በኢትዮጵያ ያላቸውን የቆይታ ጊዜ እንዲያራዝሙ በማድረግ የገቢ አቅምን የሚያሳድጉ መሆናቸውን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የገበታ ለሸገር ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ ወዲህ ቱሪስቶች ለጉብኝት የያዟቸውን ቀናት አራዝመው እየሄዱ እና የመቆየት ፍላጎት እያሳዩ ነው። በቅርቡ የሚጠናቀቁት የገበታ ለአገር ፕሮጀክቶች በቀጣይ በአገር አቀፍ ደረጃ ይህን ዕድል የሚፈጥሩ ይሆናል።

የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክትም በገበታ ለሸገር የመጣውን ለውጥ እና የተገኘውን ጥቅም በእጥፍ የሚያሳድግ ነው ብለዋል።

የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች ትልልቅ ከመሆናቸው ባሻገር በተለዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ መሆናቸውን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ይህም የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከማንቀሳቀስ ረገድ ትልቅ ፋይዳ ይኖራቸዋል ብለዋል። ፕሮጀክቶቹ በገበታ ለሸገር የመጣውን ለውጥ እና የተገኘውን ጥቅም በዕጥፍ ያሳድጋሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም አብራርተዋል።

የገበታ ለትውልድ መዳረሻዎች ለቱሪዝም ዕድገቱ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ለማወቅ የገበታ ለሸገር ፕሮጀክቶችን ማየት በቂ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ፕሮጀክቶቹ በብዙ የአገር ውስጥ እና ውጪ ቱሪስቶች መጎብኘት ከመቻላቸውም ባሻገር ቱሪስቶች የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ያስቻሉ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም በአገር ደረጃ ብዙ ኮንፈረንሶች ቢዘጋጁም ኮንፈረንሱን ለመታደም የሚመጡ ቱሪስቶች የቆይታ ጊዜያቸው በጣም አጭር ነበር። እንደ ገበታ ለሸገር ዓይነት ፕሮጀክቶች የቱሪስቶችን ቆይታ ጊዜ በማራዘም ጎብኚዎች ሊያዩ አቅደው የመጡትን ጎብኝተው እንዲሄዱ ከማድረግም ባሻገር ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ የሚያደርጉ ናቸው። የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶችም በዚህ ዘርፍ ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል።

ባለፉት ሦስት እና አራት ዓመታት ውስጥ በጎብኚዎች ላይ የታዩ ለውጦች መኖራቸውን አንስተው፤ ቱሪስቶች በጣም ደስ የሚሉ በርካታ ጊዜዎችን የሚያሳልፉበት እንዲሁም አገሪቱ ላይ ለመቆየት አቅደው ከመጡበት ቀን የቆይታ ጊዜያቸውን አራዝመው የሚመለሱበትን ውብ ቦታዎች ማፍራት መቻሉን አብራርተዋል።

ፕሮጀክቶቹ የኢትዮጵያን ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ሀብቶች መሠረት ያደረጉ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ይህም አገሪቱ ከቱሪዝም የምታገኘውን ገቢ ከፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም የተጀመሩ የገበታ ለአገር ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የቱሪስቶች ቁጥር አሁን ካለው በእጥፍ የተሻለ ይሆናል ብለዋል።

# ከሸኔ ጋር የሚደረገው የሰላም ንግግር ነገ እንደሚጀመር ተገለጸ

**ጌትነት ምህረቴ**

ከሸኔ ጋር የሚደረገው የሰላም ንግግር ነገ በታንዛኒያ እንደሚጀመር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ። የወለጋ ሕዝብ እፎይ እንዲል ሁሉም ወገን የበኩሉን እንዲያደርግም ጠይቀዋል።

የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በሂደቱ አስተዋጽኦ ላደረጉ የእውቅናና ምስጋና መርሃ ግብር ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በመርሐግብሩ ላይ መልዕክት ያስተላለፉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ ከሸኔ ጋር የሚደረገው የሰላም ንግግር ነገ ማክሰኞ በታንዛኒያ የሚጀመር መሆኑን ተናግረዋል። የኢትዮጵያን ሰላም ለማረጋገጥ እስካሁን በርካታ ተግባራት መከናወናቸውንም ገልጸዋል። ሁለት ዓመት ከመዋጋት 20 ዓመት መወያየት ይሻላልም ብለዋል።

ይህንን ቀን እንድናይ ያደረገንን ፈጣሪ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያመሰግን ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ ብለዋል። በሌላ በኩል በቀጣዩ ሣምንት



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

በብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት የተመራ ልዑክ ወደ መቀሌ እንደሚያቀናም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገልጸዋል። ልዑኩ የሁሉንም ክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች ያካተተ እንደሚሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ርዳታ ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን ለመላክ ዝግጅት ስለመደረጉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ይፋ አድርገዋል። በዚህ የዕርዳታ ማዕቀፍ 50 ሺህ ኩንታል ስንዴ ወደ ሱዳን እንደሚላክ ነው ያስታወቁት። የሱዳን ኃይሎች ለሰላማዊ አማራጭ ቅድሚያ እንዲሰጡም ጥሪ አቅርበዋል። በዚህም ጠብ አቁሞ ሰላም ለመፍጠር በቂ ያልሆነ ምክንያት እና ትክክለኛ ያልሆነ ጊዜ የለም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ሰላም ምክንያት አይፈልግም፤ ሰላም የተለየ ጊዜም አይፈልግም ብለዋል። ዛሬ እየሆነ ያለው የሰላም መቋጫ እና የአዲስ ምዕራፍ መጀመሪያ ማብሰሪያ ዕለት ነው ብለዋል። ሰላም ብርሃንና የነገር ሁሉ መጀመሪያም ነው ሲሉ ገልጸዋል። በመጨረሻም፣ ለዚህ ሰላም እንድንበቃ ላደረጋችሁን ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መልዕክት ምስጋና አቅርበዋል።

# በኦቲዝም ከምን ይሉኝ፡- ያሉትን ይበሉኝ

**መክሊት ወንድወሰን**

በኦቲዝም ክስተት ምን ይሉኝን በመፍራት መለወጥ የሚችሉ ሕፃናት ባይተዋር ሆነው፤ የስንቱ ነፍስ ሳይድንና የጉዳት ስሜት ሳይጠገን ቀርቷል። በምን ይሉኝ ይሁንታ የኦቲዝም ተጠቂዎች ተስፋቸው ጨልሞ ጉድ በጓዳ ሆኖም በማህበረሰባችን ዓመታትን ዘልቋል። ምን ይሉኝ አስተሳሰብ ባህላችን ከሆነው «ሀሜት ከመፍራት» የመጣ ነው፤ ይህ ደግሞ ማሸነፍ የሚቻለው ያሉትን ይበሉኝ የሚል ከሀሜት ነጥሮ የወጣ አስተሳሰብ መገንባት ሲቻል ነው። የምን ይሉኝ ክብር በማህበረሰባችን ቦታ ያለው ቢሆንም ቦታውን ግን ለይቶ ማወቅ ተገቢ ነው።

በቅርቡ ሻምፒዮንስ አካዳሚ ባዘጋጀው የኦቲዝም የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃግብር ላይ ተገኝተን በኦቲዝም «ከምን ይሉኝ ያሉትን ይበሉኝ» የልጃቸውን የኦቲስቲክ በሽታ በአደባባይ ተጋፍጠው ውጤት ካመጡ ወላጆች ጋር እንባን በሚያቁርና ጥርስን በሚያፈካ ስሜት ቆይታ አድርገናል።

ወይዘሮ ኩለን ኢብራሂም ልጃቸው ላይ የሚታይ የፊት የገጽታ ልዩነት አልነበረም። ነገር ግን የልጃቸው አስተዋይ መምህራን ልጁ እንደሌሎች እኩዮቹ ከሕፃናት ጋር መቀላቀል፤ አብሮ መጫወት እና የአትኩሮት ጉድለት እንዳለበት ይነግሯቸዋል። በወቅቱ መምህራኑ የነገሯቸውን አምነው ለመቀበል እንዳልፈለጉ አውግተውናል። የልጅን መጥፎ ማየትና መስማት የማይችለው የእናት አንጀት ልጃቸው የገጠመውን ችግር አምነው ለመቀበል አንድ ዓመት ፈጅቶብኛል ይላሉ።

እየዋለ እያደረ ልጃቸው ከሌሎች ልጆች ጋር መቀላቀል አለመፈለጉን በተመለከቱ ጊዜ ለማመን ተገድደዋል።

ልጃቸው ኦቲስቲክ መሆኑን አምነው በመቀበልና ካለበት ችግር ለማውጣት ሰለቸኝ ታከተኝ ሳይሉ መሥራታቸውን አጫውተውናል። ከምን ይሉኝ ያሉትን ይበሉኝ ውሳኔያቸው የልጃቸውን ክፍተት ቀርፈው ከሰዎች ጋር እንዲግባባ፤ የግል ንጽህናውን እንዲጠብቅ፣ መደበኛ የቀለም ትምህርቱን እንዲከታተል የሚያደርግ ውጤት አምጥቶልኛል ሲሉ የደስታ እንባ እየተናነቃቸው አውግተውናል።

በአገራችን የአካቶ ትምህርት መጀመሩ ኦቲስቲክ የሆኑ ልጆች ከመደበኛ ተማሪዎች ጋር በቀላሉ ተግባብተው እንዲማሩ ማድረግ መቻሉን ወይዘሮ ኩለን አጫውተውናል። ወላጆች ልጆቻቸው ያለባቸውን ችግሮች አምነው በመቀበልና የሚታገዙበትን መንገድ በማፈላለግ የልጆቻቸውን ሁኔታ በእጅጉ ማሻሻል ይችላሉ በማለት መልዕክታቸውን ችረዋል።

ሌላኛው አቶ መስፍን የልጃቸው እንደ ዕድሜ



ወ/ሮ መአዛ መንክር

እኩዮቹ ቶሎ ንግግር አለመጀመር፣ ኃይለኝነት፣ መረጋጋትና ትኩረት ማጣት አሳስቧቸው ወደ ሕክምና ተቋም እንደወሰዱት ነው የተናገሩት።

ከወለዷቸው ልጆቻቸው የተለየ ባህሪ እንዳለበት በተረዱ ጊዜ «ሳይቃጠል በቅጠል» ብለው ወደ ጤና ተቋም ልጃቸውን ይዘው ሄዱ። ልጃቸውም ሃይፐር አክቲቭ ዲስኦርደር እንዳለበት ተነገራቸው። በወቅቱ የተከሰተውን ችግር አምነው መቀበል ቢቸግራቸውም፤ በጊዜ ሂደት ችግሩን በማመን ልጃቸውን የሚረዱበትን መንገድ ማፈላለግ ተያያዙት።

ልጁ መረጋጋት ስላልነበረው ትምህርት ቤቶች ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም ሲሉ የልባቸውን አውግተውናል። መባዘናቸውን የፈታላቸው ነገር ቢኖር ልጃቸው በአካቶ ትምህርት መሳተፍ መቻሉና ለውጥ ማሳየቱ ነበር ሲሉ ተስፋና ደስታ በተደባለቀበት ስሜት ገልጸውልናል።

አሁን ይላሉ አቶ መስፍን፤ ልጁ ከበፊቱ ነገሮች ላይ ትኩረት የማድረግና የመረጋጋት ባህሪ አምጥቷል። ይህም በመምህሮቹና በቤተሰቡ ጥረት የመጣ መሻሻል ነው ብለዋል።

በስተመጨረሻም በኦቲዝም ተጋላጭ የሆኑ ልጆችን ወላጆች ከምን ይሉኝ ያሉኝን ይበሉኝ ብለው ቤት መደበቃቸውን ትተው ከባለሞያ ጋር በመሆን ችግሩ ለመፍታት መሥራት አለባቸው የሚለውን መልዕክታቸውን ለግሰዋል።

የአእምሮ ሕክምና አማካሪ የሆኑት ወይዘሮ መአዛ መንክር ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች በወላጅ ድጋፍና ጥረት ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፤ በመደበኛ ክፍል ውስጥ ገብተው የቀለም ትምህርት እንዲወስዱ ማድረግ ይቻላል ሲሉ ይገልጻሉ።

የልዩ ፍላጎት መምህራን እጅግ የበዛ ትዕግስት፣ ተነሳሽነት፤ ውዴታና ፍላጎት ሊኖራቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል። አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የመማር ማስተማሩን ሂደት የተቃና ለማድረግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸውም ብለዋል። በተጨማሪም ከልዩ ፍላጎት መምህራን ጋር መሠረታዊ ክህሎቶች እንዲዳብሩና የተግባቦት መሻሻል እንዲያመጡ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል ይላሉ።

በአገራችን በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ኦቲዝም የሚሰጠው ትርጓሜ ሃጢያት፤ የፈጣሪ ቁጣ የሚል እሳቤ ነው ሲሉ የፍቅር ኢትዮጵያ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ብሔራዊ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሸዋጌጥ ክብረት ነግረውናል። ይህንን እሳቤ ለመለወጥ ከዛሬ 16 ዓመት በፊት በፈረንጆቹ ኤፕሪል ወር የኦቲዝም የግንዛቤ ማስጨበጫ ወር ተደርጎ መሰየሙንም ነግረውናል።

በየዓመቱ ለአንድ ወር ያህል የተሳሳተን የማህበር ግንዛቤ በማስተካከል ችግሩን የመፍታት ሥራ እንደሚሠራ ገልጸውልናል። ለኦቲዝም ያለንን የተሳሳተ ግንዛቤን ለመቀየር በአገራችንም ይህ ወር የኦቲዝም የግንዛቤ ማስጨበጫ ተደርጎ በዘርፉ ያሉ በርካታ ግለሰቦች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በርብርብ እየሠሩ እንደሆነ ይናገራሉ።

ልጆች ማሕበራዊ ካልሆኑ፤ የዓይን ግንኙነት ካልፈጠሩ፤ በዕድሜያቸው መናገር ካልጀመሩ፤ አንድ ነገር ላይ ትኩረት የማድረግ አቅማቸው አናሳ ከሆነ ወላጆች ወደ ጤና ተቋማት በመውሰድ ኦቲዝም መሆን አለመሆኑን መለየት ያስፈልጋል ብለውናል።

በኦቲዝም የሕፃናት ሕክምና፣ የባለሙያዎች የተሻለ ግንዛቤ የሚያገኙበት አሠራር መዘርጋት እንደሚያስፈልግና ባለሀብቶች ትኩረት በመስጠት በዘርፉ ቢሠሩበት ችግሩን በአጭር ጊዜ መለወጥ እንደሚቻል ጠቆም አድርገዋል።

የኦቲዝም የግንዛቤ ማስጨበጫ በየአመቱ የሚሰጥ ሲሆን የዘንድሮ መሪ ሀሳቡ «የኦቲዝም ጥላ ውስጥ የሚኖሩ ወገኖችን ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን አስተዋጽኦ አድራጊ እናድርጋቸው» የሚል ነው። ይህንን መሪ ቃልም በመያዝ ወላጆች እና መምህራን ልጆቻውን ማብቃትና አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ መደገፍ እንደሚያስፈልግም ወይዘሮ መዓዛ ተናግረዋል።

ማህበረሰባችን «የምን ይሉኝ የሀሜት ፍርሀት በማስወገድ ያሉትን ይበሉኝ» እሳቤን በማጎልበት በኦቲዝም ለተጠቁ ሕፃናት አስፈላጊውን ትኩረትና እንክብካቤ ማድረግ ይገባል።



# በአፋር ክልል 196 የውሃ ተቋማት ተጠግነዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ጉዳት ከደረሰባቸው የውሃ ተቋማት መካከል 196 የውሃ ተቋማት ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን የአፋር ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ።

የአፋር ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ ሻሚ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን የውሃ ተቋማት የመለየት ሥራ ተሠርቶ ጥገና እየተደረገላቸው ይገኛል።

በክልሉ ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት 293 የውሃ ተቋማት ጉዳት እንደደረሰባቸው ያስታወሱት አቶ አህመድ፤ እስካሁን በተከናወነው የጥገና ሥራ 196 የውሃ ተቋማት አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል።

ጥገናው የተከናወነው ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ከክልሉ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ፣ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ከማህበረሰቡ በተገኘ 356 ሺህ ብር ድጋፍ መሆኑን አብራርተዋል።

በአገሪቱ ተከስቶ በነበረው የሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ቀድመው ውሃ ያገኙ የነበሩ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች የውሃ አገልግሎት የተቋረጠባቸው ሲሆን፤ እስካሁን በተከናወነው የውሃ ተቋማት ጥገና 831 ሺህ 577 ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።

ጥገና የተደረገላቸው ተቋማት ከባድ፣ መካከለኛ እና ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆኑ፤ የወደሙት ቁሳቁሶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን የሚጠይቁና ጥገናውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ከመሆናቸው የተነሳ አገልግሎት የተቋረጠባቸውን ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ እንዳልተቻለ ገልጸዋል።

በግብዓት፣ በበጀት እና ተያያዥ ችግሮች ምክንያት ለ97 የውሃ ተቋማት የጥገና ሥራ ባለመከናወኑ 239 ሺህ 256 ዜጎች የውሃ አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል ሲሉ አስረድተዋል።

የውሃ አገልግሎት የተቋረጠባቸውን ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ፣ አገልግሎት የማይሰጡትን የውሃ ተቋማት ለመስራት እና አገልግሎት እየሰጡ ያሉትን በዘላቂነት ለመስራት አንድ ሚሊዮን 467 ብር ያስፈልጋል። በመሆኑም መንግሥት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶች እና ማህበረሰቡ እገዛ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በአጠቃላይ በክልሉ የውሃ ተቋማት ላይ የደረሰው ውድመት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገቡ እና በፍጥነት ሊተኩ የማይችሉ ቁሳቁሶች ላይ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አህመድ፤ ወደ ገንዘብ ሲቀየር ከአንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ መሆኑን ገልጸዋል።

የውሃ ተቋማት እንደሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጊዜ የሚሰጠው ባለመሆኑ መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ኅብረተሰቡ እርብርብ በማድረግ ሁሉንም ዜጎች በዘላቂነት የውሃ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# በጤና መድህን አገልግሎት 56 ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል

## - 10 ሚሊዮን ዜጎች ልዩ የሕክምና ድጎማ ተደርጎላቸዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎት 56 ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት አስታወቀ። 10 ሚሊዮን ዜጎች ልዩ የሕክምና ድጎማ እንደተደረገላቸውም አስታውቋል።

በኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት የአባላት አስተዳደርና ሀብት አሰባሰብ ዳይሬክተር አቶ ጉደታ አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ላለፉት አሥርት ዓመታት የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። በአሁኑ ጊዜ ወደ 980 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በአገልግሎቱም 56 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

የጤና መድህን ኅብረተሰቡን ካልተጠበቀ የጤና ወጪ በመታደግ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ነው ያሉት አቶ ጉደታ፤ መንግሥት በየዓመቱ 25 በመቶ የሚሆነውን የአገልግሎቱን ወጪ እየደጎመ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ከዚህም ባለፈ መንግሥት 10 ሚሊዮን ከፍለው መታከም የማይችሉ ዜጎችን ልዩ ድጎማ አድርጎ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ አስችሏል ብለዋል።


አቶ ጉደታ አበበ

እንደ አቶ ጉደታ ገለፃ፤ የጤና መድህን በአገሪቱ ሀብት ላይ የተመሠረተና ቀጣይነት ያለው የሕክምና ፋይናንስ ምንጭ እንዲኖር ያደርጋል። ለዚህም በአገሪቱ ሁለት የጤና መድህን ዓይነቶች እንደሚተገበሩ አቅጣጫ ተቀምጧል። አንደኛው የማህበራዊ ጤና መድህን ሲሆን ይህም በመደበኛው ክፍለ ኢኮኖሚ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞችንና ጡረተኞችን ያቅፋል። ሁለተኛው ደግሞ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሲሆን ከመደበኛው ክፍለ ኢኮኖሚ ውጪ በገጠርና በከተማ ተሰማርተው የሚገኙ 80 ከመቶ በላይ የሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ዓላማ ለሕክምና ከኪስ የሚወጣውን ያልተጠበቀ የጤና ወጪን በማስቀረት ወደ ድህነት አረንቋ የሚገባውን የኅብረተሰብ ክፍል መታደግ መሆኑንም አክለው ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም አገልግሎቱ ለጤናው ዘርፍ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ እና በጤና አገልግሎት አስተዳደር ላይ የማኅበረሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲሁም ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ማስቻልን ያለመ ነው ብለዋል።

ጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የመመዝገቢያ ክፍያ እና መደበኛ መዋጮ መክፈል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ የእስከአሁኑ አባልነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ አዲሱ አዋጅ ስለሚወጣ አባልነት ግዴታ ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

መክፈል የማይችሉ ተብለው የተለዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወረዳ እና የክልል መንግሥት በሚያደርግላቸው ክፍያ አማካኝነት አባል እንዲሆኑ ይደረጋል ብለዋል።

# በኦሮሚያ ክልል ከበልግ እርሻ 22 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

## - 868 ሺህ ሄክታር መሬት በሰብል ተሸፍኗል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከበልግ እርሻ 22 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። እስካሁን 868 ሺህ ሄክታር መሬት በሰብል መሸፈኑ ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በዘንድሮው በልግ እርሻ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ለመዝራት እንቅስቃሴ ተጀምሯል። እስካሁን ወደ 868 ሺህ ሄክታር በሰብል ተሸፍኗል። ቀሪውም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ከዚህም 22 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

ዘንድሮ የበልግ ዝናብ ቀደም ብሎ መዝነብ መጀመሩን የገለጹት አቶ ጌቱ፤ ይህም በድርቅ የተጎዱ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የተከሰተውን የመኖና የውሃ እጥረት ችግር በመቅረፍ ላይ እንዳለ አመልክተዋል።

በዘንድሮው የበልግ ሁኔታ አሁንም ዝናቡ ቀጥሎ እየዘነበ መሆኑንና አርሶ አደሩ የክረምቱን ጨምሮ መሬትና ዘር እያዘጋጀ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ከዚህም ጥሩ ውጤት እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።


አቶ ጌቱ ገመቹ

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር የመሬት ዝግጅት ሙሉ ለሙሉ ተጠናቅቋል። ከዚህ ላይም ወደ 22 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ነው ታቅዶ እየተሠራ ያለው። በአሁኑ ወቅትም አንዳንድ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ መሬቶች ወደ እርሻ እየገቡ ሲሆን፤ በዚህም የተሻለ ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል።

ዋና ዋና ምርት ተብለው የሚታወቁ በበልጉ ወቅት ይዘራሉ ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በክልሉ በበልግ አብቃይ ዞኖች በበልጉ ወቅት ለስንዴ ምርት ትልቅ ትኩረት መሰጠቱን ገልጸዋል። ወደ 296 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ እንዲሁም ከ130 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ደግሞ በበቆሎ ምርት እንደሚሸፈንም አስታውቀዋል። የጥራጥሬ እህሎችና ገብስም እንደየአካባቢው ሁኔታ እየተዘሩ እንዳለ አመላክተዋል።

በበልጉ ወቅት ያለው ዝናብ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ፤ ማዳበሪያን ጨምሮ የግብርና ግብዓቶች በተያዘላቸው ጊዜ ለተጠቃሚው አርሶ አደር መድረሱን፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በአርሶ አደሩ በኩል ማዘጋጀት እንደተቻለ እና የምርት አቅርቦትም በስፋት እንደተሰራጨ የቢሮ ኃላፊው ተናግረዋል።

የቢሮ ኃላፊው፤ አጠቃላይ የክልሉን የግብርና ሥራ ሜካናይዝድ ለማድረግም ከአለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል። በዚህም በየጊዜው የኩታ ገጠም እርሻ እየጨመረ መምጣቱንም ጠቁመዋል።

የሜካናይዝድ እርሻውን ለማስፋፋት ባለፉት ሁለት ዓመታት ከስድስት ሺህ በላይ እንዲሁም በዚህ ዓመት ብቻ 700 የሚሆኑ ትራክተሮች ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ተችሏል ነው ያሉት።

በበጋም ይሁን በመስኖ ምርትን «በኮምባይነር» የማጨድ ሥራም እንዲሁ በስፋት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በመኸር ወቅት ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በትራክተር እንደታረሰና ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነው ምርት በኮምባይነር መሰብሰቡን አስታውሰዋል። ይህም በየዓመቱ እየጨመረ እንደሚሄድ ገልጸዋል።

ዜና

# በትግራይ ክልል በተያዘው ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ ይጀመራል

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል በጦርነቱ ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የመማር ማስተማር ሂደት ለማስጀመር በቀጣይ ሳምንት በሁሉም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምዝገባ የሚካሄድ መሆኑን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ዳኘው አይጠገብ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በትግራይ ክልል በጦርነት ምክንያት ለሦስት ዓመት ተኩል ገደማ ትምህርት ተቋርጦ ቆይቷል። በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሠረት አንፃራዊ ሰላም የተፈጠረ በመሆኑ በክልሉ ከሚያዝያ 18 ጀምሮ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምዝገባ ይጀመራል።

ትምህርት ሚኒስቴር በክልሉ ትምህርት ለማስጀመር እያደረገው ያለው መልካም ተግባርና ጥሩ ተነሳሽነት የሚደነቅ እንደሆነ የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ሚኒስቴሩ ቡድን በመላክ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱ መሥራቱን ተናግረዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ የተመራ ቡድን መቀሌ በመገኘት ትምህርት እንዲጀመር የሚያስችል ሥራ ሲሠራ መቆየቱን በማንሳት፤ በዚህም የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

በተለይ ችግሮች የሚፈቱበትን መንገድ በመለየት የትምህርት ሚኒስቴር ትኩረት ሰጥቶ ለማገዝ የሚያስችለውን አቅጣጫ ነድፎ ወደ ሥራ መግባቱን ገልፀዋል።

እንደ አቶ ዳኘው ገለፃ፤ ከጊዜያዊ አስተዳደሩ ጋር በመተባበር በክልሉ ትምህርት ለማስጀመር ሁለንተናዊ ዝግጅት ተጠናቋል። ከቅድመ አንደኛ ክፍል (ኬጂ) እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርት ይጀመራል። በተለያየ ምክንያት የተበታተኑ መምህራንን የማሰባሰብ ሥራ ለማከናወንም ራሱን የቻለ ወጥ ሰነድ ተዘጋጅቷል። የነበረው የደመወዝ አለመከፈል ችግር እንዲፈታ እና ወደ ትምህርት እንዲገባም ውሳኔ ላይ ተደርሷል።

በክልሉ ላይ የተፈጠረው ችግር ከባድ ከመሆኑ አንፃር በክልሉ ትምህርት ቢሮ ብቻ ለመፍታት ያዳግታል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሁሉም አካላት ለትግራይ ክልል እገዛ ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል።

# የኢትዮጵያ ግዙፍ ኢኮኖሚ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ጀማል መሐመድ፤ ቻይናን እንደ አብነት በመጥቀስ አንዲት አገር ግዙፍ ኢኮኖሚ ገነባች ማለት ለዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች ትልቅ ገበያ ተፈጠረ ማለት ነው ይላሉ። በቻይና እያንዳንዱ ግለሰብ ድሃ ሆኖ እያለ፤ የተወሰነ ኢኮኖሚዋ ማንሰራራት ሲጀምር፤ የአሜሪካና የአውሮፓ ኩባንያዎች ተሻምተው ቻይና ገበያ ላይ ኢንቨስት ማድረግ መጀመራቸውን ያስታውሳሉ።

ቻይና ብዙ ሕዝብ ስላላት የአሜሪካ፣ የኳታርንና የዴንማርክን ባያክልም በብዛት ማምረት ስትጀምርና በርካታ ኩባንያዎች ወደ አገሪቱ ሲገቡ ከፍተኛ ገበያ ሆኖ መመዝገቡን ያነሳሉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤትነትም በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ትልቅ ገበያ እንደሚፈጥር ያምናሉ።

«ባለፉት 20 ዓመታት ኢኮኖሚው እያደገ ነው ስንል ብንቆይም አብዛኛውን ሕዝብ ተጠቃሚ ስላላደረገ የሚቀረው ነገር እንዳለ ያመላክት ነበር» የሚሉት ዶክተር ጀማል፤ የተመዘገበው ውጤት የዜጎችን ኑሮ ከመቀየር አንጻር ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ይገልጻሉ። ቻይና በሕዝብ ብዛት ቀዳሚ አገር በመሆኗ ዓለም ላይ ካሉት የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤቶች አንዷ እንደሆነችው ሁሉ፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው የአፍሪካ አገራት አምስተኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ለመቻሏ የሕዝብ ብዛቷ አዎንታዊ ሚና እንዳለውም ይጠቅሳሉ።

«በኢትዮጵያ ትልቅ ኢኮኖሚ ተፈጠረ ማለት የማምረትና የመግዛት አቅም ከፍተኛ ይሆናል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ኤክስፖርት ማድረግ ይቻላል» ይላሉ ዶክተር ጀማል። አክለውም «ሌሎች አገራት ከኢትዮጵያ ምርት በስፋት መጠቀም ይጀምራሉ። በሚፈጠረው ምቹ ሁኔታም ሌሎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ማምረትና መሸጥ እንዲችሉ ያደርጋል። በሌላ በኩል የዜጎችን የኢኮኖሚ ሁኔታም የሚያሻሽል እንደሚሆን ተስፋዎች እንዳሉ ያሳያል» በማለት ያብራራሉ።

እንደ ዶክተር ጀማል ማብራሪያ፤ የተገኘው ውጤት የኢኮኖሚውን ጥራት ሙሉ ለሙሉ አሻሽሎታል ማለት ያስቸግራል። ነገር ግን ይነስም ይብዛም እያንዳንዱ ሰው አምርቶ የሚገባ በመሆኑ ለኢኮኖሚው ማደግ አበርክቶ አለው። አሁን በተመዘገበው ውጤት ኢትዮጵያ ትልቅ ገበያ ትፈጥራለች። ለኢንቨስተሮችም ምቹ አጋጣሚ ይፈጠራል።

ዶክተር ጀማል፤ በቱሪዝም ሴክተር ላይ፣ በፓርክ ኢንቨስት የተደረጉና የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለኢኮኖሚው እድገት አበርክቶ እንዳላቸው ያምናሉ። የድሃውን ሕይወት መቀየር ላይ ግን ገና ይቀራል ባይ ናቸው። ከዚህ አንጻር ግብርናውንም፣ የአምራች ኢንዱስትሪውንም የሚዳስስ ውጤት ማምጣት ይገባል ሲሉም ይመክራሉ። የተጀመረውን የክላስተር ግብርና ማስፋት፣ በተለይም ሀብት ባለባቸው አካባቢዎች ላይ በስፋት መተግበር እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ቀደም ሲል የኢትዮጵያን አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት 126 ቢሊዮን ዶላር እንደሚሆን ያስቀመጠው የአይ.ኤም.ኤፍ ትንበያ ዳግም ሲከለስ ወደ 156 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ከፍ እንዲል አስችሎታል። በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያ ጎረቤት አገር ኬንያን በልጣ ከአፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው አገራት አንዷ መሆን ችላለች። ናይጄሪያ በ506 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ቀዳሚ ስትሆን ደቡብ አፍሪካ ደግሞ በ399 ቢሊዮን ዶላር እንደምትከተል ነው ትንበያው የሚያመላክተው።

እንደ አይ.ኤም.ኤፍ ትንበያ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገቱን በመቀጠል እ.ኤ.አ 2028 የቀጣናው ቀዳሚ ግዙፍ ኢኮኖሚነቱን ይዞ የሚቆይ ሲሆን፤ ይህም በተለይም በግብርናና በማኑፋክቸሪንግ ልማት ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን የመሳብ አቅሟን ለአገሪቷ ከፍ ለማድረግ ምቹ አጋጣሚን ይፈጥራል።

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የዋና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ የተገኘውን ውጤት አስመልክተው ሲናገሩ፤ ኢኮኖሚውን ይበልጥ ለማጠናከር፣ የፓርቲውን የጉባዔ አቅጣጫዎች በውጤታማነት ለመፈፀምና በ10 ዓመቱ ዕቅድ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ጠንካራ ሥራ እየተሠራ መሆኑን እንደማሳያ ያነሳሉ። በቀጣይም አጠናክረን እንደምንቀጥል በተለያዩ ማሳያዎች ለሕዝቡ ማረጋገጥ ይኖርብናል ሲሉም ተናግረዋል። ይህም ፓርቲው ቃል የገባውን በተግባር ማረጋገጥና ፈተናዎችን ወደ እድል መቀየር መለያው መሆኑን ያመላክታሉ።

በኢኮኖሚ ዘርፍ ካስቀመጥናቸው ግቦች መካከል በ10 ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያን ከአፍሪካ አምስት ጠንካራ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች መካከል አንዷ እንድትሆን ማድረግ ይገኝበታል ያሉት የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ ግባችንን አስቀመጥን ወደ ሥራ ከገባን ገና ሦስት ዓመት ቢሆነንም ከወዲሁ ስኬታችን መታየት ጀምሯል ሲሉ ይገልጻሉ። ብልጽግና ቃል የገባውን በተግባር ማረጋገጥና ፈተናዎችን ወደ ዕድል መቀየር መለያው ነው የሚለውን የአቶ አደምን ቃል አጽንኦት ይሰጡበታል።

የኢኮኖሚ ዋና ዓላማ ድህነትን መቀነስ፤ ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግና የኑሮ ደረጃን መቀየር ነው የሚሉት ዶክተር ጀማል በበኩላቸው፤ ድህነትን መቀነስ ካልተቻለ ኢኮኖሚውን ዘላቂ ማድረግ እንደማይቻል ይገልጻሉ።

የኢኮኖሚ ለውጡ ሲጀምር ሁሉም በአንድ ተሳታፊ ላይሆን ስለሚችል አዳዲስ ክህሎትና መሠረታው ለውጥ ማምጣት እንደሚያስፈልግ፤ የኢኮኖሚ መነቃቃት ሁልጊዜም ቢሆን አሽጋጋሪ ነገሮች በተቋማት ደረጃ መፈጠር እንዳለባቸው፤ ቴክኖሎጂን በስፋት ማላመድ እንደሚገባ አንስተው ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ተስፋው ባለበት ይቀራል በማለት ዶክተር ጀማል ስጋታቸውን አስቀምጠዋል።

# «ኢትዮጵያ ከነበረችበት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሁለት ዓመት ከመዋጋት 20 ዓመት መወያየት እንደሚሻል ገልጸው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ችግሮቻችንን በውይይትና በምክክር መፍታት የስልጣኔ ሀሁ እንደሆነ መገንዘብ አለብን ሲሉ ገልጸዋል።

ከተበላሸው ይልቅ ያማረ፣ የተዋበና ተስፋ የሚሰጥ ነገር መፍጠር እንችላለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ትናንትን ተሻግረን ለነገ የተሻለ ነገር ለመፍጠር የምንሠራና የምንተጋ መሆን ይጠበቅብናል ብለዋል።

ዛሬ ይቅርታና ዕርቅ ስለሆነ ወደ ኋላ የተበላሸውንም ማረም፣ የተሰበረ መጠገን፣ የቆሰለን ማከም የተቸገረን መደገፍ፣ ትናንትናን በተሻለ ፍቅር ማደስና ማስቀጠል የሚችል መሠረት መጣል እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ ኢትዮጵያውያን በጦርነት ጀግኖች እንደሆንን ዓለም ይመሰክራል፤ በሰላም ጀግኖች ለመሆን የተጎዳው ሁሉ ወገኔ ነው ብለን መደገፍ ይኖርብናል ነው ያሉት።

በሰላም ሂደቱ ተሳትፎ ለነበራቸው አካላት ሁሉ እውቅና በመስጠት ምስጋናቸውንም ያቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከጦርነት ወጥተን በሰላምና መልሶ ግንባታ ላይ እየተነጋገርን በመሆኑ የዛሬው ዕለት ለኢትዮጵያ ልዩ ቀን ነው ብለዋል።

«ከምክር ይልቅ መከራ የሚያስተምረን መሆን ስለሌለበት የጦርነትና የመከራ ጊዜ አብቅቶ፤ ትናንትን ተሻግረን ለነገ የተሻለ ለመሥራት መዘጋጀት አለብን» ብለዋል።

ከጦርነት ወጥተን በሰላምና መልሶ ግንባታ ላይ እየተነጋገርን በመሆኑ ዕለቱ የተለየ ቀን መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይ በብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት መሪነት የሁሉም ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ወደ መቀለ ይጓዛሉ ሲሉም ተናግረዋል።

ሰላማችንን በትብብርና አብሮነት ኢትዮጵያን በፅኑ መሠረት ላይ አኑረን ማስቀጠል አለብን ብለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ግጭት በሰላም ስምምነት እንዲቋጭ ቁልፍ ሚና ለነበራቸው አካላት የምስጋና እና የዕውቅና ሰርተፊኬትና ስጦታ አበርክተዋል።

በመርሐግብሩ ላይ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽነር ሙሳ ፋቂ ማሃማት፣ በሰላም ስምምነቱ የተሳተፉ አካላት፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንንን ጨምሮ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ዲፕሎማቶችና ሌሎች እንግዶች ታድመዋል።



የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ናሌዲ ፓንዶር

# የአፍሪካ አገራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬኒያታ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የተከናወነው ሥራ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ ኩራት መሆኑን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የሚፈለገው ሰላም እውን ሆኗል፤ በመሆኑም በግጭት ውስጥ ያሉ የአፍሪካ አገራት በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ችግር ከተፈታበት መንገድ ትምህርት በመውሰድ ሰላም ማምጣት አላባቸው ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አፍሪካ ለራሷ ችግሮችን በራሷ መፍትሄ ማምጣት እንደምትችል በተግባር አሳይታለች ያሉት የቀድሞው ፕሬዚዳንት፤ በኢትዮጵያ የመጣው ሰላም ለመላ አፍሪካውያን ጥሩ ተምሳሌት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ነው ያሉት።

መጪው ጊዜ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና አጠቃላይ ለአፍሪካ ዘላቂ ሰላምና ብልጽግና እውን እንዲሆን እመኛለሁ። ለሰላም ጥረት ያደረጋችሁ ሁሉ እና መላ ኢትዮጵያውያን እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።

የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ናሌዲ ፓንዶር በበኩላቸው በአፍሪካ ኅብረት መሪነት የተደረሰው የሰላም ስምምነት የኢትዮጵያውያን ድል ብቻ ሳይሆን እንደ አፍሪካውያን የሁላችንም ኩራት ነው ብለዋል። የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ኢትዮጵያ ቅኝ ያልተገዛች አፍሪካዊት አገር ብቻ ሳትሆን በሰላም ረገድም አርአያነትን ያረጋገጠችበት አጋጣሚ መሆኑን ተናግረዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ጦርነት የተፈታበት መንገድ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ መፍትሄ መቅረፍ እንደሚቻል ያረጋገጠ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የፕሪቶሪያ ሰላም ስምምነት የመንግሥትና የሕወሓት አመራሮች ወደ ሰላም ለመምጣት ቁርጠኛ አቋም ማሳየታቸውን አስታውሰው፤ አፍሪካ ኅብረትን እና ሂደቱ እንዲሳካ ሚና የተወጡ አካላትን አመስግነዋል፡፡ የሰላም ስምምነቱ ስኬት ወረቀት ላይ መፈረሙ ሳይሆን በተግባር መሬት ላይ ያለው ትግበራ መሆኑን ያወሱት ሚኒስትሯ፤ የድሕረ ሰላም ስምምነት ትግበራው ላይ ባደረጉት ክትትል የሰላም ስምምነቱ አፈጻጸም በጥሩ ደረጃ እየተተገበረ መሆኑን ማረጋገጣቸውን አንስተዋል።

በቀጣይም ትግበራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለመከላከያ ሰራዊትና ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል። ስምምነቱ ዘላቂ ሰላም፣ ልማትና አንድነት ለማምጣት የተገባ ቃል በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ሁሉም ወገኖች በቁርጠኝነት እንዲሠሩም አሳስበዋል።

መሰል የሰላም ሂደቶች አፍሪካ በአጀንዳ 2063 የበለጸገች፣ ሰላሟ የተረጋገጠ፣ አካታች እና ዘላቂ ልማት የተረጋገጠባት አህጉር የማድረግ ግብ እንዲሳካ ሁነኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አንስተዋል።

በመርሐ ግብሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳፋኪ ማሃማት፣ በአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ፣ የደቡብ አፍሪካ የዓለም አቀፍ ግንኙነት እና ትብብር ሚኒስትር ናሌዲ ፓንዶር እና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢኮኖሚውን ከኮንትሮባንድ የሚታደግ መልካም ተግባር!

የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር የተለያዩ ስልቶች ተነድፈው እየተሰራ መሆኑን ተከትሎ ብዙ ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ምርቶችን መያዝ እየተቻለ ነው። የጉምሩክ ኮሚሽን በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ብቻ 52 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ሸቀጦችን መያዝ የቻለበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል። ይህ የኮንትሮባንድ ሸቀጥ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ እንዲሁም ከሀገር ወጥቶ ቢሆን ሀገርና ሕዝብ በእጅጉ ይጎዱ ነበር።

ኮሚሽኑ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አሰራሮችን በመቀየስ ውጤታማ ተግባር እያከናወነ መሆኑን ይገልፃል፤ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውም በዚያው ልክ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን እየጠቆመ ይገኛል። በስድስት ወሩ የታየውን የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን አስደንጋጭ ብሎታል። 52 ቢሊዮን ብር የሚደርስ የኮንትሮባንድ ሸቀጥ መያዝ መቻሉ ትልቅ ነገር ሆኖ ፣ ይህን ያህል የኮንትሮባንድ ሸቀጥ በህገወጦች እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ሲታሰብ ችግሩ በራሱ ምን ያህል አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በሚገባ ይጠቁማል።

የኮንትሮባንድ ንግድ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለመድረሱ የጉምሩክ ኮሚሽን የተለያዩ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችን ዋቢ ያደረጉ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎችም ያመለክታሉ። በየጊዜው የሚወጡት እነዚህ ዘገባዎች በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመቱ የኮንትሮባንድ ሸቀጦች እየተያዙ ስለመሆናቸው ያሳያሉ። የጉምሩክ ኮሚሽን እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያካሂዷቸው መድረኮች ላይም የችግሩ አሳሳቢነት እየተጠቀሰ ይገኛል።

ጉዳዩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ተጠቁሟል። በቅርቡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት እንደተናገሩት፤ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በወጪ ንግዱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳረፈ ይገኛል። የዘንድሮው የወጪ ንግድ አፈጻጸም ከአምናው ጋር ሲነጻጸር ትንሽ ዝቅ ብሏል። ዘንድሮ ለውጭ ገበያ ከቀረበው ወርቅና ጫት የተገኘው ገቢም ከአምናው ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅ ብሏል።

አሶሳ ላይ ባለፈው ዓመት ወደ ማእከላዊ ገበያ 20 ኩንታል ወርቅ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ዘንድሮ ግን ሶስት ኩንታል ነው የቀረበው። ይህ ማለት አብዛኛው በህገ ወጥ መንገድ ሄዷል ማለት ነው፤ ወርቅ እያመረትን ወደ ማዕከላዊ ገበያ ከማምጣት ይልቅ በአሻጥርና ኮንትሮባንድ ወደ ጎረቤት ሀገሮች በስፋት ይሄዳል። ታንታለም ጉጂ ይመረታል፤ ይሁንና ኢትዮጵያ ኤክስፖርት ከምታደርገው በላይ የማያመርቱት ጎረቤት ሀገሮች ኤክስፖርት ያደርጋሉ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለችግሩ አሳሳቢነት አስገንዝበዋል።

ይህንን በኮንትሮባንድ እንቅስቃሴው እያጋጠመ ያለውን ችግር ለመከላከል አብዛኛው ኃይላችን አሁን ሀብት ባለባቸውና ሽፍታ በበዛባቸው አካባቢዎች እንዲሰፍር ተደርጓል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ፣ የፌዴራል ፖሊስ ቀዳሚ ተግባር ኮንትሮባንድን መዋጋት በኮንትሮባንድ የሚመዘበረውን የኢትዮጵያን ሀብት መከላከል ይሆናል ሲሉ ማስታወቃቸው ይታወሳል።

የጉምሩክ ኮሚሽን የኮንትሮባንድ ንግዱን ለመቆጣጠር የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ እያከናወነ ያለው ተግባርና ይህን ተከትሎም እያስገኘ ያለው ለውጥ በአርአያነት የሚጠቀስ ነው። ይሁንና ተቋሙም እንዳለው የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውም ፈታኝ እየሆነ መጥቷል። ይህን ፈተና ለማለፍ የመከላከል አቅምን አጎልብቶ ከመገኘት በተጨማሪ የኅብረተሰቡን፣ የክልል አስተዳደሮችንና የጸጥታ ኃይሎችን ርብርብ ማጠናከርም ይገባል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር ተግባር የመከላከያ እና የፌዴራል ፖሊስ ቀዳሚ ተግባር ይሆናል ባሉት መሰረት እነዚህ ኃይሎች የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውን መቆጣጠር ውስጥ መግባታቸው ኢኮኖሚውን እየተስፋፋ ከመጣው የኮንትሮባንድ ንግድ ለመጠበቅ ፋይዳው የጎላ ይሆናል።

የኮንትሮባንድ ተግባሩ እየተስፋፋ ከመጣ ጤናማነቱ ሁሌም አጠያያቂ የሆነው የሀገሪቱ የንግድ እንቅስቃሴ ይበልጥ ታማሚ እንዲሆን ያደርጋል። ሀገርና ሕዝብም ለዋጋ ንረት፣ የምርት ጥራት ጉድለት እንዲስፋፋ፣ ህጋዊ ነጋዴዎች ቀስበቀስ ከገበያ እንዲወጡ በማድረግ በአጠቃላይ የንግድ ስራው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳርፋል። ይህ ሁኔታ በንግዱ ማኅበረሰብ እና በአጠቃላይ በሸማቾች ላይ ከሚያሳርፈው ችግር በተጨማሪ የሀገር ኢኮኖሚም ችግር ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል።

ይህም ችግሩን ለመቆጣጠር ርብርብ ማጠናከር ላይ ማተኮርን የግድ ይላል። ኅብረተሰቡ፣ የክልል መስተዳድሮች፣ ሌሎች የኮንትሮባንድ መከላከል አካላት ኮንትሮባንድን የመከላከልና መቆጣጠር ስራቸውን ይበልጥ ማጠናከር በሚኖርባቸው ወቅት ላይ መሆናቸውን በመገንዘብ መስራት ይኖርባቸዋል። እነዚህ አካላት ኮንትሮባንዲስቶች ሊያቀርቧቸው በሚችሉ መደለያዎች ሳይበለጡ እንዲሰሩ በሚያስችሏቸው የስነ ምግባር መርሆች ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል።

ከመረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው በኮንትሮባንድ ተግባሩ እየተንቀሳቀሰ ያለው ሀብት ከፍተኛ ነው። ይህ ሀብት በህገወጥ መንገድ የተገኘ ነው። ኮንትሮባንዲስቶች ይህን ሀብት ለመጠበቅ የማይከፍሉት ዋጋ እንደማይኖር በመገንዘብ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር የተቀናጀ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ለዚህም የሕዝቡን ፣ በየደረጃው ያለውን የመንግስት የአስተዳደር እርከን፣ የጸጥታና የደህንነት ኃይሎችን አቅም በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው። መንግስት የሀገር መከላከያንና የፌዴራል ፖሊስን ለዚህ ተግባር ለማሰማራት የያዘው ቁርጠኛ አቋምም ተገቢም ወቅታዊም ነው። ይህ ኢኮኖሚውን ከኮንትሮባንዲስቶች ሊታደግ የሚችል ተግባር ውጤታማ እንዲሆንም የሕዝቡና የክልል አስተዳደሮች የቅርብ ድጋፍ ወሳኝ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ከሀገር የተሻገረ ፣ ለአፍሪካውያን የተሰጠ እውቅና

ዘካርያስ

ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ያለው የኢትዮጵያ መንግስት አዲስ ባህል ይዞ መጥቷል። ይህ ባህል የምስጋና ወይም የእውቅና ባህል ነው። በዚህም ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ተቋማት፣ ወዘተ ላከናወኗቸው መልካም ተግባሮች ልዩ ስነ ስርአት በማዘጋጀት እውቅና ይሰጣል። በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ የእውቅና መርሀ ግብሮች ለሀገር የዋሉ የመከላከያ ሰራዊትና የፖሊስ አባላት፣ ባለሀብቶች፣ ዲያስፓራዎች፣ ጠንካራ ግብር ከፋዮች፣ ሰራተኞች፣ አመራሮች፣ ቡድኖች፣ ወዘተ. እውቅና ተሰጥቷቸዋል፤ ተመስግነዋል፤ ተበረታትተዋል።

ለእነዚህ አካላት ላባረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ማቅረብ አንድ ትልቅ ነገር ነው፤ ስራቸው ዋጋ እንዳለው ሀገርና ህዝብን የጠቀመ መሆኑን ከፍተኛው የመንግስት አካል አውቆላቸዋል፤ መንግስት ለእነዚህ አካላት ማድረግ የሚችለውን ትልቁን ነገር ነው ያደረገው። ይህ እውቅና በአደባባይ የሚከናወን፣ ለህዝብ ይፋ የተደረገ፣ ከገንዘብም ከንብረትም በላይ ነው።

እውቅናው ሌሎችም ይህን አርአያነት ያለው ተግባር እንዲከተሉ ግንዛቤ የሚሰጥበትም ነው። እነዚህ ተምሳሌቶች እንዲበዙ፣ እንዲበረክቱ ለማድረግም አቅም አለው። ይሄ እውቅና ምን ያህል ሌሎች መሰል ጀግኖችን እንዳፈራ ለማወቅ ጥናት ወይም መሰል ተግባር ማከናወንን ቢጠይቅም፣ ሌሎች ተመሳሳይ ጀግኖች ማፍራት እንደሚያስችል ግን ጥርጥር የለውም። እውቅና መሰጠቱ እውቅና ተቀባዮችን አበረታትቶ ብቻ አይቆምም፤ ሌሎችም በእነሱ ልክ ተነቃቅተው እንዲሰሩ በር ይከፍታል።

የእውቅና መርሀ ግብሮች በተለያዩ ደረጃዎች በብዛት በተደጋጋሚ እየተካሄዱ ይገኛሉ፤ በፌዴራል መንግስት ደረጃ ብቻ ሳይሆን፣ በክልሎች፣ ከዚያም በታች ባሉ እርከኖችና በተለያዩ ድርጅቶች ወይም መስሪያ ቤቶች ተመሳሳይ መርሀ ግብሮች በተደጋጋሚ ይካሄዳሉ። ይህ ሁሉ ሁኔታ የሚያመለክተው እውቅና እየተሰጠ ያለበት ሁኔታ ሌሎች ለመልካም ስራ እንዲተጉ እያነሳሳ መሆኑን ነው።

መንግስት ይህን ታላቅ መርሀ ግብር ከሀገር ለተሻገረ ተግባርም አውሎታል። የእውቅና ባህሉን በዛሬው እለት ደግሞ ለሌላ ከፍ ያለ ተግባር ያውለዋል። ከሀገር ለተሻገረ ተግባር አውሎታል። በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄደው ጦርነት በሰላም ስምምነት እንዲጠናቀቅ ላደረጉት የአፍሪካ ልጆች ምስጋና ያቀርብበታል።

የአፍሪካን ልጆች ለማመስገን የሚካሄደው ይህ የምስጋና ባህል ለብቻው ትርጉሙ ብዙ ነው። እንደሚታወቀው፤ ኢትዮጵያ ላለፉት አመታት ህልውናዋን አደጋ ላይ በጣለ ጦርነት ውስጥ ቆይታለች። ከሕወሓት ጋር በተደረገው በዚህ ጦርነት የአያሌ የኢትዮጵያውያን ህይወት ጠፍቷል፤ አካል ጎድሏል፤ የዜጎች ሰላምና መረጋጋት አደጋ ውስጥ ገብቷል፤ የሀገር ሀብት ወድሟል፤ የሀገር ገጽታ በእጅጉ ተበላሽቷል። ሀገር በአንዳንድ ዘርፎች የወደሙባትን ንብረቶች ተከትሎ አዲስ ጎጆ ወጪ የሆነችበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ጥፋት እንዳይቀጥል ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱ የአፍሪካ ልጆች የተሰጠ እውቅና ነው።

በወቅቱ የነበረውን ጦርነትና በሀገሪቱ ውስጥ፣ ዙሪያዋን እና በተለያዩ የኢትዮጵያን ጥሩ በማይመኙ ሀገሮች ሲደለቅ የነበረውን የጦርነት ነጋሪት እየሰሙ ኢትዮጵያ ልትበተን ነው፣ የሊቢያ፣ የመን፣ የኢራቅ እጣ ፈንታ ሊደርሳት ነው እያሉ ሲያሟርቱ የነበሩ ኃይሎች ሟርት ያከሸፈ የሰላም ስምምነት እንዲደረስ ያደረጉ አፍሪካውያን በኢትዮጵያ መንግስት በይፋ እውቅና ማግኘታቸው የህፍረት ማቃቸውን እንዲከናነቡ ያደርጋቸዋል።

አንዳንድ ምእራባውያን ኃያላን ሀገሮች ኢትዮጵያ ላይ ያሳረፉት ጫና ዛሬም ድረስ ሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ቋት አሟጦታል፤ የአሜሪካ መንግስት የኢትዮጵያ መንግስትን ያንበረክክልኛል ያለውን አሜሪካ ለኢትዮጵያ በአጎአ የሰጠቻትን ከቀረጥ ነጻ መብት ማገዱ በኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ባለሀብቶችና ምርቶቻቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳርፏል። ሀገሪቱ በኢንዱስትሪ ፓርኮቿ የያዘቻቸው እቅዶች በታሰበው ልክ እንዳይሄዱ ተደርገዋል።

ይህ ደግሞ ኢኮኖሚዋን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሻገር በምትታትር ሀገር ላይ ሊያሳድር የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ መገመት አይከብድም። በደቡብ አፍሪካ ከዚያም በኬንያ ለተደረሱ ስምምነቶች የአፍሪካውያኑ አቀራራቢነት ዋጋው ከፍተኛ ነውና እውቅናው በእርግጥም ይገባቸዋል፤ ይመጥናቸዋል።

ለእዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነው ጦርነት ተዋናዮችን ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት እንዲመጡ በማድረግ ከዚያም ለስምምነት እንዲደርሱ ላደረጉ፣ በስምምነቱም መሰረት መሬት ላይ ነገሮች እንዲፈጸሙ በማድረግ በኩል ታሪክ ሲያስታውሰው የሚኖር ተግባር ላበረከቱ የአፍሪካ ልጆች የኢትዮጵያ መንግስት የምስጋና መርሃ ግብር ማዘጋጀቱ ለሰላም ያለው ጽኑ አቋም ተጠናክሮ መቀጠሉ በሚገባ የታየበት፣ ለሰላም ዋጋ ለሚከፍሉ ሁሉ ያለውን ታላቅ ክብር ያሳየበት እንደመሆኑ ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል።

የሰላም ስምምነቱ የዜጎችን እልቂት፣ አካል መጉደል፣ መሰደድ፣ ከእንግልት ፣ ሴቶችን ከአስገድዶ መደፈር የሚታደግ፤ በጦርነት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ መኖርን የሚያስቀር ጥሪታቸውን፣ ሀብታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ የሚያስጠብቅ እንደመሆኑ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፤ በተለያዩ ወገኖች ዘንድ አድሮ የነበረውን የሀገር ገጽታ ስብራት ይጠግናል፤ ያድሳል፤ ይህ የሰላም ስምምነት እንዲደረስ ለታተሩ፣ ስምምነቱ መሬት እንዲያርፍ ለደከሙ የአፍሪካ ልጆች መንግስት ይህን ታላቅ መድረክ በማዘጋጀት እውቅና መስጠቱ አሁንም የመንግስትን የሰላም ቁርጠኝነት በሚገባ ያመለክታል።

የሰሜን ኢትዮጵያውን ጦርነት ተፋላሚዎች ለማደራደር ሌሎች ወገኖችም ሞክረዋል። አሜሪካና የአውሮፓ ህብረት ከእነዚህ መካከል ይጠቀሳሉ። ማደራደሩ ባልከፋ፤ እነዚህ ሀይሎች በወቅቱ ያራምዱ ከነበረው አቋም አኳያ በማደራደሩ ጉዳይ ይኖራቸዋል ተብሎ ከታሰበው ወገናዊነት አኳያ ሚናቸው አዋጭ እንዳልሆነ ተገምቷል።

የኢትዮጵያ መንግስት ግን ችግሩ አፍሪካዊ ነው ፤ መፍትሄውም በአፍሪካውያን እጅ ነው ብሎ አፍሪካውያን ለችግሩ መፍትሄ እንዲያመጡ በማሳወቅ በሩን ለአፍሪካውያን አደራዳሪዎች ከፍቷል። ይህን የኢትዮጵያ መንግስትን ጽኑ አቋም የተገነዘበው የአፍሪካ ህብረት ለሽምግልናው በተከፈተው በር ገባ። ህብረቱ ለእዚህ ታላቅ ጉዳይ የቀድሞውን የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሊሰጉን ኦባሳንጆን ሰየመ። እሳቸውም ወደ ኢትዮጵያ ብዙ ተመላለሱ፤ ትግራይ ክልልም እየተመላለሱ ጥረት አደረጉ።

የሰላም ውይይቱ በደቡብ አፍሪካ ሊካሄድ መሆኑ ሲሰማ ደግሞ በሰላም ውይይቱ ላይ የደቡብ አፍሪካና የኬንያ ፕሬዚዳንቶች ተካተቱ። አፍሪካዊ ጉዳይ መሆኑ በግልጽ እየታየ መጣ፤ አፍሪካውያኑ እንደሚጠበቁትም አፍሪካዊ መፍትሄ አፍልቀው ሁለቱ ወገኖች ፊት ለፊት እንዲነጋገሩ አደረጉ። እነዚያ በመገናኛ ብዙሃን ሲካሰሱ፣ በጦር ግንባር ሲጫረሱ የነበሩ ወገኖች ሲወያዩ ሰነበቱ፤ ከሰላም ስምምነትም እንዲደርሱ አደረጉ።

ሁለቱ ወገኖች ንግግራቸውን ሲያደርጉም በሌሎች ሀገሮች እንደታየው ውይይት የተቋረጠበት፣ ገባ ወጣ የበዛበት ሁኔታ አልታየም፤ የተኩስ አቁም የተጣሰበት ሁኔታም አልነበረም፤ ብዙዎች እንደጠበቁት ባለመስማማት መለያየት አልተስተዋለም። ይህም ውይይቱ የይስሙላ ሳይሆን የልብ መሆኑን ያመላከተ ነው። ከቀናት ውይይት በኋላ ስምምነት ተደረሰ። በኬንያ የተካሄደው ውይይትም እንዲሁ ሰላማዊ በሆነ መልኩ ነው የተካሄደው።

ይህ ስምምነት የተደረሰው ግጭት በሚጠመቅባት አፍሪካ ውስጥ ነው። የአያሌ አፍሪካውያንን ህይወት የሚቀጥፉ፣ ሀብትና ንብረታቸውን እያወደሙ ለድህነት እንዲዳረጉ የሚያደርጉ አያሌ ግጭቶች በሚቀፈቀፉባት፣ ግጭቶቹ መፍትሄ አልባ ሆነው አመታትን በሚዘልቁባት አፍሪካ የተደረሰ የሰላም ስምምነት እንደመሆኑም ስምምነቱ ለአፍሪካም ልዩ ስፍራ ያለውና ሞዴል ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው ነው። ይህን ላደረጉ የአፍሪካ ልጆች እውቅና መስጠት በእጅጉ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት ተግባር ነውና የኢትዮጵያ መንግስትም ሊመሰገን ይገባዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የቆዳ ምርቶች ለፋሽን ኢንዱስትሪው ዕድገት

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የፋሽን ዲዛይን አሁን አሁን በስፋት እየተዋወቀ የመጣ ዘርፍ ነው። በተለይም በሀገር ውስጥ በሚመረቱ የጨርቃጨርቅ ምርቶች፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች እንዲሁም የእደጥበብ ውጤቶችን በመጠቀም እጅግ ውብና ማራኪ በሆኑ ዲዛይኖች የተለያዩ አልባሳት ይመረታሉ። እነዚህ አልባሳት ታድያ በቀደመው ጊዜ ለአልባሳት ሲውሉ እምብዛም አይስተዋሉም ነበር። አሁን ላይ ግን በተለይም የቆዳ ምርቶች ለፋሽን ኢንዱስትሪው ድምቀት ከመሆን ባለፈ በሥራ ዕድል ፈጠራና በውጭ ምንዛሪ ግኝት ጉልህ ድርሻ እያበረከቱ ይገኛሉ።

ከሰሞኑ 13ኛው የመላው አፍሪካ አለም አቀፍ የቆዳ ንግድ ትርዒት በሚሊኒየም አዳራሽ ተካሂዶ እንደነበር ይታወሳል። የዝግጅት ክፍላችንም ይህንኑ ትርዒት ለመታደም በቦታው በተገኘበት ወቅት እጅግ ውብ የሆኑ የእጅ ሥራዎች በቆዳ ላይ አርፈው ተመልክተናል።

ከመግቢያ በር ጀምሮ ወደ ውስጥ ስንዘልቅ አይንን አፍዝዘው የሚያስቀሩ በአማረ ዲዛይን የተሰሩ የቆዳ ውጤቶች አይተናል። ከግራ ወደ ቀኝ በማለት በአግራሞት ካስተዋልናቸው የቆዳ ምርቶች በተጨማሪ በአዳራሹ የፋሽን ትርዒት የሚያሳዩ ሞዴሎች ቀልብ ይስቡ ነበር።

ሞዴሎቹ በተለያየ ቀለምና ዲዛይን ከቆዳ የተሰሩ አልበሳት እንዲሁም ጫማ ተጫምተዋል። አልባሳቱም ሆነ ጫማዎቹ በሞዴሎች ሰውነት ላይ ሲታዩ ቀልብ የሚስቡ ናቸው። በቃላት የማይገለጽ ውበት ያላቸው እነዚህ የቆዳ ውጤቶች በአገር ልጆች ተሰሩ ለማለት ይከብዳል። ይሁንና ዲዛይነሮቹ ያማረ ሥራቸውን ይዘው ቀርበዋል።

የፋሽን ትርዒቱን ካዘጋጁት አካላት መካከል የፋሽን ትርዒት አቅራቢዋ ማህሌት ተክለማርያም አንዷ ናት። ማህሌት የፋሽን ትርዒት በማዘጋጀት ረጅም ልምድ አላት። በዚህ በመላው አፍሪካ የቆዳ ኢግዚቢሽን ላይ ያሉትን ምርቶች በሞዴሎች አማካይነት ማቅረብ እንደቻለች ገልጻለች።

እሷ እንዳለችው የፋሽን ትርዒት የቆዳ ምርቶችን ፋሽን ለማስተዋወቅ የቀረበ ነው። በዕለቱ ከጠዋት ጀምሮ ሞዴሎችን በማልበስ በፋሽን ትርዒት መልኩ አልባሳትን እንዲያሳዩ በማድረግ የቆዳ ምርቶችን በደንብ ማስተዋወቃቸውን ትናገራለች። ይህ ደግሞ የቆዳ ምርቶችን ኤክስፖርት ለማድረግ ትልቅ ሚና አለው።

በርካታ የሀገር ውስጥ አምራቾች በልብስ፣ በጫማና በቦርሳ ብዙ የተለያዩ ፋሽኖች ዲዛይን ያደርጋሉ የምትለው ማህሌት፤ በፋሽን ትርዒቱም ዘመነ አሞር ፣ ሜሮን አዲስ አበባ፣ ሩት ስታይል፣ ኬሬዥ፣ ታፋ እና ሌሎችም አቅራቢዎች ተሳታፊ መሆናቸው ገልጻለች። ኦስሞን ዲዛይን ደግሞ ለፋሽን ትርዒቱ የሚሆኑ ሙሉ ልብሶችን ከጫማዎቹ ጋር ዲዛይን በማድረግ ማቅረቡን ትናገራለች።

ይህ የፋሽን ትርዒት የተዘጋጀበት ዋና ዓላማ ምርቶቹን ለማስተዋወቅ እንደሆነ የምትገልጸው ማህሌት፤ የቆዳ ኢንዱስትሪው እንዲበረታታ የሀገር ውስጥ ሸማቾች የቆዳ ምርቶች መሸመት እንዳለበቸው ትናግራለች። ምርቶቹ ጥራታቸውን ጠብቀው የተዘጋጁ መሆናቸውን ጠቅሳ፣ ምርቶቹ በብዛት ወደ ውጪ ሀገራት ኤክስፖርት የሚደረጉ ቢሆኑም በሀገር ውስጥ በርካታ የመግዛት አቅም ያለው ሰው ምርቶቹን ገዝቶ መጠቀም አለበት ብዬ አምናለሁ ትላለች።

‹‹ሀብ ኦፍ አፍሪካ›› በሚል በየዓመቱ የሚዘጋጅ የፋሽን ትርዒት ስለመኖሩ ያነሳችው ማህሌት፤ አሁን ላይ የፋሽን ኢንደስትሪው ትርጉም ያለው ለውጥ እያሳየ እንደሆነ ነው የገለጸችው። የፋሽን ትርዒት በፋሽን ኢንዱስትሪው ሆነ በሞዴሎች ላይ ያለው አመለካከት ለመለወጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን አንስታ፤ ልብሱ ተለብሶ ሲቀርብ ከሚሰጠው ደስታ ባሻገር ትልቅ ገቢ የሚያስገኝ ኢንዱስትሪ መሆኑንም ነው የገለጸችው።

አሁን ላይ የቆዳው ዘርፍ ማህበራት ይህንን ትርዒት በማዘጋጀት ከውጭ ሀገር ካሉ አካላት ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲካሄድ ማድረጋቸው በሀገር ውስጥ ማምረት እንደሚቻልም ያሳዩበት አንዱ መንገድ ነው። በቀጣይም ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ እንዲህ ያሉ ዝግጅቶችን በማድረግ ማስተዋወቅና ማበረታታት ይገባልም ብላለች ።

ሰዓሊና የፋሽን ዲዛይነር አቶ ኦስማን መሐመድ በበኩሉ፤ በፋሽን ትርዒቱ አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ፣ ቡድን ባለው የልብስ አሠራርና ፈጠራ የታከለባቸው ጫማዎችና አልባሳት ዲዛይን አድርጎ ማቅረቡን ይናገራል።

የፋሽን ዲዛይን ሥራዎች ከሌላው ለየት ያሉ መሆናቸውን ሲገልጽ ‹‹ዲዛይኑን ስሰራ የተመሰጥኩበት፣ መሠረት ከሆንኩባቸው ነገሮች በመነሳት ታሪክ በመስጠት ነው የምሰራው። እያንዳንዱ ልብስ ታሪክ አለው፤ እንደታሪካቸው ሁሉ ቀለማቸው ወቅቱን የጠበቀ ሆኖ ይሰራል። ልዩ የሚያደርጋቸው ደግሞ ሙሉ ማሽን ሳይነካቸው በእጅ ብቻ የሚሰሩ መሆናቸው ነው፤ በተለይ ጫማዎቹ›› ይላል ።

ሙያውን ወዶትና ከውስጡ በመነሳት የሚሰራው ስለሆነ በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደሚወደድለትም ይናገራል። በመሆኑም በፋሽን ትርዒቱ ላይ አልባሳቱም ሆኑ ጫማዎቹን ያዩትም ሆነ ለብሰው ያሳዩት ይማረኩበታል። አልባሳቱም ሆነ ጫማዎቹ እራሳቸው የሚያወሩ፣ አይነት ታሪክ ያላቸው እንደሆኑም ተናግሯል።

አቶ ኦስማን እንደሚለው፤ የሥራዎቹ ለውጭ ገበያ ቅርብ የሆኑ አይነት ዲዛይን ያላቸው ናቸው። ውጭ ሀገር ፈጠራ የተሟላበት ነገር የማድነቁም ሆነ ባለቤት የመሆኑ እድል የበለጠ ነው። እኛ ጋ ግን እይታው በራሱ አዲስ ነው። ልብሶች ላይ ያለው እይታ የሚያነቃቃ ነው፤ ግድብ ያለ ስሜት የለውም፤ ደስታና ነፃነትን ያሳያል ።

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ዓለም አገራት በፋሽን ዲዛይን ለየት ያለው ፈጠራ የታከለበት ተፅእኖ ፈጣሪ ዲዛይነሮች በመስራት መሸለሙን የሚናገረው ኦስማን፤ በፋሽኑ ተፅእኖ መፍጠር ማለት አንድ የሚሰራ ልብስ የራሱ የሆነ ታሪክ ሊኖረውና የሚታዩ ነገሮች ሁሉ ወደ ሀሳብ ተቀይረው ውጤት ማምጣቱ ማሳየት ሲቻል ነው ይላል።

ከዚህ በተጨማሪ አነጋጋሪ የሆነ ሥራን ሰርቶ ወጣ ብሎ ማየትን፣ ሰፋ አድርጎ ማሰብን ድፍረትን የሚጠይቅ መሆኑን በመግለጽ፤ በዚህ ሥራ ላይ በቆዳ ብዙ ነገር መፍጠር እንደሚቻልም ለማንፀባረቅ እንደሞከረ ነው ያስረዳው።

አቶ ኦስማን የፋሽን ዲዛይኑ እንዲህ አይነት መድረክ ሲፈጠርለት የገበያ ትስስር ከመፍጠር በዘለለ አዲስ ነገር በየጊዜው የማስተዋወቅ በየዓመቱ አእምሯአችንን መፍጠር የሚችለውን ሥራ ጥግ ድረስ መጠቀም እንዲችል ያግዛል ይላል። ይህ ማለት ደግሞ የሥራ እድሉንም የሚጨምርና የቆዳ ኢንዱስትሪ ላይ ሲባክን የነበረውን ያስቀራል። ታይቶ ያልታወቀው ነገሮች እንዲታዩና የልምድ ልውውጥ እንዲኖርም እድል ይፈጥራል ሲል ያብራራል።

‹‹ከውጪ የሚገቡ ( ኢንፖርት) የተደረጉ ልብሶችም ሆኑ ጫማዎችን መጠቀም ሁልጊዜ ፍላጎታች ነው›› የሚለው ኦስማን ፤ በፋሽን ዲዛይን ኢንዱስትሪው ከተለመደ ውጭ የሆነ የተሻለ ሥራ እንዲሠራ እና ኤክስፖርቱ እንዲሰፋ ለማድረግ እንዲህ አይነት መድረክ ትልቅ እድል ይፈጥራል በማለት ሀሳቡን አጠቃሏል። እንደዚህ አይነት ኤግዚቢሽኖች ደግሞ እርስ በእርስ በማስተዋወቅ አንዱ ከአንዱ ልምድ እንዲቀስም እድሉን ይፈጥራል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ዕውቀት ለምን ወደ ሥልጣኔ አልወሰደንም?

**ዋስልኝ አየለ**

በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚጠቀሱ ሦስት ደረጃዎች አሉ። ዕውቀት፣ ክህሎት እና አስተዋይነት(attitude)። ሦስተኛውን ደረጃ(attitude) በትክክል ሊገልጸው የሚችል የአማርኛ አቻ ቸገረኝ፤ ብዙም ሲባልበትም አንሰማም። ጥቅል ትርጉሙ ግን ከዕውቀት(knowledge) እና ክህሎት(Skill) በኋላ የሚገኝ አስተዋይነት፣ ሥልጡንነት፣ ብልህነት፣ አርቆ አሳቢነት፣ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ የሥልጣኔ ደረጃ የሚመጥን አስተሳሰብ መገንባት ማለት ነው።

ዕውቀት ስለአንድ ነገር ማወቅ ነው፤ ክህሎት ደግሞ ባወቅነው መሰረት አንድን ነገር እንዴት እንደሚሰራ(ቴክኒካል ነገሩን) መተግበር መቻል ነው። አስተሳሰብ(attitude) ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ነው። ሦስቱን ደረጃዎች ለመግለጽ፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ አንድ የስነ ዜጋና ስነ ምግባር መምህር የሰጠንን ምሳሌ ልጠቀም።

ደን ለሰው ልጅ የሚሰጠውን ጥቅም(አፈር እንዳይሸረሸር ማድረግ፣ ንፁህ አየር እንድንተነፍስ ማድረግ፣ ለዝናብ መፈጠር....) ማወቅ ዕውቀት ነው። ችግኝ ማፍላትና መትከል ደግሞ ክህሎት ነው። ደን እንዳይጨፈጨፍ ግንዛቤ መስጠት፣ ዛፎችን ልክ እንደ ሰው ሕይወት ማየት... የመሳሰሉት ደግሞ አስተሳሰብ(attitude) ናቸው።

በሦስቱ ደረጃዎች መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለብን ችግር የአስተሳሰብ ነው። በጭንቅላት የመሰልጠን ችግር አለብን። በተለምዶ ግን ‹‹አለማወቅ›› እየተባለ ይገለጻል። ያለማወቅ ችግር አይደለም ያለብን፤ የመሰልጠን ነው።

በነገራችን ላይ ሥልጣኔ በቁስ አካል ብቻ አይደለም፤ በአስተሳሰብ መሰልጠን ነው። ሥልጣኔ ሲባል ለብዙዎች ትዝ የሚለው ዘመናዊ ዕቃዎችን መጠቀም፣ የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎችን መጠቀም እና እንደ አገር ደግሞ የፎቆችና አስፋልቶች መብዛት ነው። አዎ! እነዚህ የሥልጣኔ መለያዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በአስተሳሰብ ካልተሰለጠነ በአብረቅራቂው ሕንጻ ሥር ባለ ቆሻሻ ምክንያት አፍንጫ ተይዞ ነው የሚታለፍ። በረቀቀው ቴክኖሎጂ የብልፅግና ቃላት ነው ስንለዋወጥበት የምንውል።

ሥልጣኔን የገጠር ሰዎች የሚጠቀሙት አንድ ቃል የሚገልጸው ይመስለኛል። ‹‹እገሌ እኮ ሥልጡን ነው›› ይላሉ። ይህን የሚሉት በቁስ አካላዊ ሁኔታው አይደለም፤ በአስተሳሰቡና አመለካከቱ ነው። ለምሳሌ፤ ሰው የማይሳደብ፣ ትህትና ያለው፣ ረጋ ብሎ የሚያዳምጥ፣ ሰው የሚጎዱ ነገሮችን የማያደርግ ሰው ‹‹ሥልጡን›› ይሉታል። እንዲያውም ‹‹ሥልጣኔ›› የሚለውን ቃል በሕብረተሰብ ትምህርት ከማወቄ በፊት ‹‹ሥልጡን›› የሚለውን ቃል ነበር የማውቀው። ስለዚህ ሥልጣኔ ማለት ሥልጡን ዜጋ መፍጠር ነው።

አገራችን አሁን ያለችበት የጦርነትም ሆነ የድህነት ጣጣዎች የተፈጠሩት በአስተሳሰብ ባለመሰልጠናችን ነው። በ19ኛው ክፍለ ዘመን በተፈጠሩ ክስተቶች ዛሬ ላይ የምንጣላው በአስተሳሰብ መጥቀ መሄድ ስላልቻልን ነው። ከሠለጠኑ አገራት መማር ስላልቻልን ነው። የአውሮፓ አገራት የሥልጣኔ ምሳሌ የሚደረጉት በቁስ አካል ብቻ አይደለም፤ በአስተሳሰባቸው ነው። ከመቶ ምናምን ዘመናት በፊት በተፈጠሩ ነገሮች ስለማይጣሉ ነው። ዛሬ ላይ ሰላማዊ ኑሮ የሚኖሩ በአስተሳሰባቸው ሰልጥነው እንጂ የእርስበርስ ጦርነትን ለዓለም ያስተማሩት እኮ እነርሱ ነበሩ!

እውቀት ብቻውን ሥልጣኔ አያመጣም። ስለዓለም ጓዳና ጎድጓዳ ማወቅ ብቻውን አገር አያሳድግም። የነጭ ሳይንቲስቶችን ንድፈ ሀሳብ መሸምደድ ብቻውን ሥልጣኔ አይደለም። የግሪክ ፈላስፎችን ጥቅስ መደርደር የምሁርነት መገለጫ አይሆንም። ለሥልጡንነት ዋናው ነገር በአስተሳሰብ መሰልጠን ነው።

ከዚህ በፊት የገለጽኩት አንድ ትዝብት ነበር። በትልልቅ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉ ሠራተኞች የተማሩ የሚባሉ ናቸው። በዚህ ዘመን ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ከ12ኛ ክፍል በታች አይሆንም፤ አብዛኛው የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ ነው። ስለግል እና አካባቢ ንጽህና የምንማረው ከሙአለ ሕጻናት ጀምሮ ነው። አንዳንዶቹ ሠራተኞች ደግሞ መምህር ሆነው ያገለገሉ ናቸው።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን በመጸዳጃ ቤቶች ውስጥ የምናየው ነገር ‹‹አጃኢብ!›› የሚያሰኝ ነው። ማስተዋል የሚባል ነገር የለም። መቼም ምግብ የሚበላው በአንድ እጅ ነው አይደል? መጸዳጃ ቤት ውስጥ ያለውን መታጠቢያ ምግብ ባልበሉበት እጅ መክፈት ያን ያህል ውስብስብ ነገር ነው? ወጥ በነካ እጅ ሰዎች የሚገለገሉበትን ነገር መንካት አይከብድም? ተሳስተው ከነኩትስ በዚያ ልክ ወጥ በወጥ ሆኖ ሲያዩት ማጠብ እንዴት ትዝ አይልም?

ምግብ ቤት ውስጥ የተሰጣቸውን ብርጭቆ ወጥ በነካው እጃቸው የሚጨብጡ አሉ። የብርጭቆው ወገብ ወጥ በወጥ ይሆናል። ምናለ በዚያኛው(ወጥ ባልነካው) እጃቸው ቢይዙት?

እነዚህን ጥቃቅን ነገሮች እንደ ማሳያ ያመጣሁት አገራዊ ችግር የሚያመጡ ሆኖ አይደለም፤ ግን ምን ያህል ከሥልጣኔ የተጣላን መሆናችንን ያሳያል። ሰዎች የሚገለገሉበትን ነገር ማበለሻሸት እንኳን የተማረ ከሚባል ከማንኛውም የሰው ልጅ ፍጡር አይጠበቅም።

እነዚህ ጥቃቅን ግዴለሽነቶቻችን እያደጉ ሄደው ነው በትልልቅ ጉዳዮችም ችግር የሚፈጠረው። ግዴለሽነት፣ የራስን ጥቅም ብቻ ማስቀደም፣ ነገ ምን ሊያስከትል እንደሚችል አለማስተዋል አገርን ወደኋላ ይጎትታሉ።

ከላይ የጠቀስኳቸው ትዝብቶች ሁሉ በዕውቀት ችግር የሚከሰቱ አይደሉም። አሳቢ ባለመሆን የሚከሰቱ ናቸው። ቆሻሻ መንገድ ላይ የሚጥል ሰው ‹‹ጉንፋን ከምን ይመጣል?›› ቢባል ምናልባትም የሳይንስ ማጣቀሻዎችን እየዘረዘረ ሊተነትን ይችላል። የበሽታዎችን መንስኤና መከላከያ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ያውቃል፤ ዳሩ ግን ማሰብ የሚባል ነገር የለም።

የሰለጡኑት አገሮች አንዱ የሥልጣኔ መለያ ህግ አክባሪነት ነው። ሰዎችን የሚጎዳ ነገር አይደረግም። ሰዎች ያለመረበሽ መብት አላቸው። መቼ ነው ይህን ሥልጣኔ የምንገነባ?

ሥልጣኔ አመለካከት ነው። ሥልጡን ዜጋ መፍጠር ነው። የምናየው ግን ተደራራቢ የትምህርት ማዕረግ ይዘው ምስኪን ለፍቶ አዳሪ አስተናጋጅ ሲሳደቡ ነው። ለምሳሌ ያዘዙት ምግብ ላይ ጨው ቢበዛ አስተናጋጇን ነው አበሻቅጠው የሚሳደቡ። እንዲያውም ባለቤቱ ሲመጣ ተቅለሰልሰውና ተለሳልሰው ‹‹ትንሽ ጨው በዝቶበታል!›› ሊሉ ይችላሉ፤ ወይም ‹‹በጣም ጥሩ ነው!›› ሊሉ ይችላሉ። ምስኪኗ ሰራተኛ ላይ ግን ይደነፋሉ። ይሄ በአስተሳሰብ አለመሰልጠን ነው።

አገልግሎት ለማግኘት የሚደረግ ሰልፍ ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ? ሰልፍ ያስፈለገው በሰዎች አመጣጥ ቅደም ተከተል በሥነ ሥርዓት ለመገልገል ነው፤ ዳሩ ግን አገልግሎቱ ሲጀመር ለረጅም ሰዓት የቆየው ሰልፍ ድብልቅልቁ ይወጣል። በሥነ ሥርዓት መሆኑ ቀርቶ በጉልበት ይሆናል። የሥልጣኔ ዘመን መሆኑ ቀርቶ የጥንቱን የአደን ዘመን ይመስላል።

የአስተሳሰብ ለውጥ ካልመጣ የቱንም ያህል የትምህርት ደረጃ ቢደራረብ ከኋላቀርነት አያድንም፤ የሰለጠነ ዜጋ አይፈጥርም። ስለዚህ ዕውቀታችን ለመሰልጠን ይሁን!

# የሰላም አምባሳደር በመሆናቸው እናመሰግናለን

**ታምራት ተስፋዬ**

የታሪክ ተመራማሪና የፍልስፍ አዋቂው ፕሮፌሰር ዩቫል ኖህ ሐረሪ አለማችን ካፈራቻቸውና ድንቅ ስራዎችን ካበረከቱ ምሁራን መካከል በበርካቶች ዘንድ በግንባር ቀደምትነት ስማቸው ይጠቀሳል። እስራኤላዊው ፕሮፌሰር በተለይም Sapiens /ሳፒየንስ/ እና 21 Lessons for the 21st Century በሚል ባሳተሟቸው መፅሐፍ ይበልጡን ይታወቃሉ። ፕሮፌሰሩ ሁለተኛ ላይ በተጠቀሰው ስራቸው በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ ሊማርባቸው ይገባል ብለው ከዘረዘሯቸው 21 ነገሮች ውስጥ ጦርነት አብላጫውን ቦታ ይወስዳል።

ፕሮፌሰሩ እኤአ በ2018 ባሳተሙት በዚህ መፅሃፉ የጦርነትን አስከፊነት በጥልቀት ከመተንተን ባሻገር የሰው ልጅ በታሪኩ ካሳለፋቸው ጦርነቶች ሊማር ግድ ስለመሆኑና በጦርነት ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደሌለ መለስ ብሎ መቃኘት እንደሚገባ አፅእኖት ይሰጡታል።

እንደ እርሳቸው ሁሉ የጦርነትን አስከፊነት በሚመለከት በርካቶች ፅፈዋል። ስለ ሰላም ብዙዎች ዘምረዋል። አዚመዋል። አያሌዎች ህይወታቸውን ሰውተዋል። በሁሉም ባህሎችና እምነቶች እንዲሁም ሕዝቦች ዘንድ ሰላም ከፍተኛ ዋጋ አለው። ሰላምን የማያስተምር እምነት የለም። በየቤተ እምነቱ በሚደረጉ ፀሎቶችም ሰላም ከቀዳሚ ርዕሶች አንዱ ነው። ህዝብም እንደ የእምነቱ ፈጣሪን እለት እለት በሰላም ያሳደርከኝ በሰላም አውለኝ ከማለት አልፎ፤ ስለ አገሩ ሰላም ይፀልያል። ይማፀናል።

ስለ ሰላም ሲነሳ የቀድሞው ዩናይትድ እስቴትስ ተወዳጅ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን አባባል ሁሌም ይታወሳል። አባባሉም «ሠላም ማለት ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ መፍታት መቻል ማለት ነው» የሚል ነው። እርግጥም ሠላምን በጉልበት ማስጠበቅ አይቻልም። ሠላምን ማሳካት የሚቻለው በመግባባት ብቻ ነው።ልዩነትን ማቀራረብ ወይም ቅራኔን ማርገብ የሚቻለው በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ እንጂ፣ «የምፈልገውን አስፈጽማለሁ»በሚል ጀብደኝነት አይደለም።በተለይ በፖለቲካው አለም ፉክክርና የትግል ተሳትፎ ሁለናተናዊ ሰላም እውን ይሆን ዘንድ ከአገርና ከሕዝብ በፊት ሥልጣንን ማስቀደም፣ከራስ ክብርና ዝና በላይ ለሌላው አለመጨነቅና ዕብሪት አሽቀንጥሮ ማስወገድ የግድ ይላል።

ሰላም የሚረጋገጠውም በሠለጠነ አስተሳሰብ እንጂ ዘመን ባለፈበት አስተሳሰብና በጠመንጃ አምላኪነት አይደለም። ለአገር የሚበጅ ሥርዓት ዕውን ሊሆን የሚችለው በሕዝብ ይሁንታ እንጂ በጀብደኝነት አይደለም።ሆኖም አያውቅም። በኋላ ቀር አስተሳሰብ ተቸክሎ ጠመንጃ መወልወልም ሆነ ውረድ እንውረድ ተባብሎ ጦር መስበቅ፣ በየትኛውም መመዘኛ በጣም የሚያስንቅ አስነዋሪ ድርጊት ነው።

ሰላምን በጉልበት የማምጣት ሙከራዎችም በአብዛኛው ትርፋቸው መከራ ነው። በጉልበትና በጠመንጃ የሚጠበቅ ሰላም ቀኝ ጠብቆ ፍርክርኩ መውጣቱ አይቀሬ ነው። አንዳንድ ፀሐፍት እንዳውም በጉልበት የተገኘ ድል ከሽንፈት እኩል ያነፃፅሩታል።ምክንያታችን የሚሉት ደግሞ ጊዜያዊ መፍትሄ መሆኑን ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ በቀደሙት አመታት አንድ ችግር ሲያጋጥና ሰላም ሲደፈርስ ተነጋግሮ መፍትሔ ለማፍለቅ ከመትጋት ይልቅ ዱላ መምዘዝ የተለመደ ነው።በዚህም ምክንያት ግጭትን ወይም ጦርነት ሙጥኝ በማለት ዓላማን ለማስፈጸም ጥድፊያው ሲበረታም ይታያል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አመታት ጦርነት ባስከተለው ሁለንተናዊ ቀውስ ከባድ መንገራገጮችን ወይንም shocks ውስጥ ቆይታለች። በጦርነቱ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ሞተዋል። በርካቶች ከአካላዊና ከሥነ ልቦናዊ ጉዳት በተጨማሪ ከሞቀ ጎጃቸው ተፈናቅለዋል። ግምቱ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የህዝብ እና የአገር ሀብት ወድሟል።

> እናት ኢትዮጵያ ስትጣራ አቤት በማለት አገሪቱን የተበተቡ ሰንሰለቶችን በጣጥሰዋል። የተቆለለባትን የሴራ ተራራ ንደዋል። ምሬቷን በሀሴት ቀይረዋል። መከፋቷን በደስታ ለውጠዋል። ዝቅታዋን ለሚመኙ ከፍታዋን አሳይተዋል።ወዟን ከሚነጥቁ ውበቷንም ከሚሰርቁ ቀማኞች ታድገዋታል

የሰሜን ጦርነት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ባለፉት ሁለት ዓመታት ጦርነቱ ኢኮኖሚውን እያደቀቀ የዜጎችን ኑሮ ከማክፋቱና የሚሊዮኖችን ደኅንነት ከማቃወሱም በላይ ኢትዮጵያ ብዙ ሴራ ተሸርቦባታል። በርካታ መሰናክሎች አልፋለች።ተወንጅላለች።በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሚዲያዎች ሆን ተብሎ ገጽታዋ እንዲጠቁር ተደርጓል። ተስፋ ቢስ እንደሆነች ተደርጋም ተስላለች።

እንደሚታወቀው፣ ጦርነቱ ብዙ ብዙ መልኮችን፣ወዳጅ ጠላትን አሳይቶናል። የኢትዮጵያ ጭንቀት የሚጨንቃቸው ህመሟ የሚያማቸው አገራትና ተቋማትንም አስቃኝቶናል።ከዚህ በተቃራኖ የዓለም የሰብዓዊ ሞራል አስጠባቂነትን ካባ ለራሳቸው የደረቡ አገራት፣ጥቅማቸውን ለማስከበር እስከምን ሊሄዱ እንደሚችሉና ትክክለኛ ተፈጥሯቸውን በተጨባጭ አስመልክቶናል።

የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብም ለመሰል የውጭ ተፅእኖዎች ሳይንበረከክ፣ የሰላም ንግግር ሐሳብን በዋናነት ሲደግፉና እንዲጀመርም ከፍተኛ ግፊት ሲያደርጉ ቆይቷል።ከብዙ ጥረት በሰላም በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ሥር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የሰላም ንግግር እውን ሆኗል።የኢትዮጵያን ጥቅምና ክብር ባስጠበቀ መልኩ ሰላምን እውን ለማድረግ ከስምምነት ተደርሷል።

ይህም የሰላም መንገድ ለኢትዮጵያ ትልቅ ድል ነው:: በሰላም እንጂ በጦርነት ያተረፈ ሀገር አለመኖሩን በመረዳት ግጭትና ጦርነት ይብቃን መባሉ እጅግ የሚደገፍና የሚያስደስት ነው:: በሠለጠነ አካሄድ የሰላም መንገድ ማራመድም ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው።

ከውጭ አገራት አሸማጋዮች ይልቅ እኛው ለእኛው በሚል መርህ መከወኑ ደግሞ በተለይ የአፍሪካ አገሮች ከምእራባውያን ይልቅ በራሳቸው አቅም ያለማንም ጣልቃ ገብነት ከቅኝ ግዛት እሳቤ ተላቀው የራሳቸውን ችግር በራስ መፍታት እንደሚችሉ ተጨባጭ ምሳሌ የመሆን ትርጉሙን ያልቀዋል።

የሰላም አየር መተንፈስ መጀመሩ በተለይ ኢትዮጵያ የታሪካዊ ጠላቶቿ መቀለጃና መፈንጫ እንዳትሆን ያደርጋል። በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እጃቸውን አስረዝመው የሚያስገቡ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት እንዳይሳካ ግዙፍ ሚና ይጫወታል። ይህን ከግምት ከማስገባት በጦርነቱም ወቅት የታለፉ የጨለማ መንገዶችን ማስታወስ በቂ ነው።

በእኔ እምነት እነዚህ ለሰላም አስተዋፅኦ ያደረጉ አካላት ለኢትዮጵያውያን ትልቅ ክብር ያላቸው ናቸው። ኢትዮጵያ ተሻሽላና አድጋ ማየት የሚፈልጉ፣አንድ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንድትኖር ከልብ የሚመኙና ለዚያም የሚታገሉ ናቸው። የሚኖሩት በእሷ ተከብሮ መቆየት ውስጥ ነው። እርሷ ሰላሟን አጥታ ሕሊናቸው አትረጋጋም።ኢትዮጵያ ጎድሎባት እነርሱ አይሞላላቸውም።እርሷ ዝቅ ብላ እነርሱ አይገዝፉም።የሚኖራቸው አገራቸው ሲኖራት ነው።

የሰላም ተዋናዮቹ በተግባራቸው የማንነትና የኢትዮጵያዊነት ትርጉም ፍቹ ቅኔና ወርቁ ነፃነት መሆኑን አሳይተዋል። ሰላም ሲሆኑ ከውብም በላይ አስፈሪ መሆናቸውንና የችግራቸው ግዝፈት በአብሮነት እንደሚቀል፣አቅማቸው ከአብሮነታችን የሚመነጭ ጥንካሬአችው እንደሆነ አረጋግጠዋል።እንደ ሴረኛውና ሸራቢው፣ እንደ ሟርተኛውና ፈራጁ ኢትዮጵያ ከውጭም ከውስጥም ፈተና ሲበዛ የምትደክም፣ ህዝቦቿም የሚንበረከኩ ለሚመስላቸው ትልቅ መልእክትን አስተላልፈዋል።

ለዚህ ስኬትም ቀድሞው የናይጀሪያ ፕሬዚዳንት እና የአፍሪካ ህብረት ልዩ መልእክተኛ ኦሊሴንጎ አባሳንጆ ፣ የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፣ የአፍሪካ ህብረት፣ የኢትዮጵያና የሕወሓት የድርድሩ ተወካዮች እንዲሁም ስመጥር ግለሰቦች ሚና መቼም ታሪክ የማይዘነጋው ነው።

እነዚህ የሰላም አምባሳደሮች እናት ኢትዮጵያ ስትጣራ አቤት በማለት አገሪቱን የተበተቡ ሰንሰለቶችን በጣጥሰዋል። የተቆለለባትን የሴራ ተራራ ንደዋል። ምሬቷን በሀሴት ቀይረዋል። መከፋቷን በደስታ ለውጠዋል። ዝቅታዋን ለሚመኙ ከፍታዋን አሳይተዋል።ወዟን ከሚነጥቁ ውበቷንም ከሚሰርቁ ቀማኞች ታድገዋታል።

ዛሬ ላይ ሰላም የተገኘውም«የከፉ ቀን ደራሽ፣ የአገር ባለውለታ እና ቆራጥ ጀግኖች ህይወትና አካል ተገብሮበት ነው። ለእናት አገር ፍቅር የሚከፈለው መስዕዋትነት የዋዛ የሚታይ አይደለም።ከሕይወት መስዋዕትነትና በአካል ላይ ከሚደርስ ጉዳት በተጨማሪ፣የአገር ፍቅር ስሜት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገርበት የነፃነት ተጋድሎ መገለጫ ጭምር ነው።

ለእነዚህ የኢትዮጵያን እድገት እንጂ ዝቅታዋን፣ ደስታዋን እንጂ ሃዘኗን፣ ክብሯን እንጂ ውርደቷን ፈፅሞ የማይመኙ የቁርጥ ቀን ልጆች ብሎም ተቋማት ተገቢውን ክብር እውቅና መስጠትም እጅግ የሚያስመሰግን ተግባር ነው። እውቅናው አገራቸውን ለሚወዱ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በእውቀት፣ በገንዘብ፣ በደም እና በሕይወት ዋጋ ለከፈሉ ሁሉ ማስታወሻ ነው። እውቅና መስጠት ላበረከቱት አስተዋፅኦ፣ ማበረታታት፣ መደገፍ፣ ማድነቅ ትርጉሙ ላቅ ያለ ነው።

መሰል የእውቅ መርሀ ግብሮችን ማካሄድ ነገ ጠብን ከማቀጣጠል ይቀል ስለ ሰላም የሚደክሙ እንዲፈጠሩ ይግዛል።ያበረታታል።ጉልበት ይሆናል።ይህ ከሆነማ ነገ እኔም እሸለማለሁ፣ እታወሳለሁ ብሎ ስለ ሰላም ክብር እንዲያስብ ብሎም እንዲጨነቅ ያደርጋል።

በዛሬ ተግዳሎ ሁሉ አልፎ ታሪክ ሆኖ ሲወሳም ለነገው ትውልድ የሚያስተላልፈው መልእክት ግዙፍ ነው። በትውልድ ቅብብሎሽ ኢትዮጵያዊነት ታላቅነት አልሸነፍ ባይነት መሆኑን ከማስረገጥ ባሻገር ትውልዱ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ያስተምራል።ከሁሉም በላይ እውቅናው በመድረኩ ለተጠሩት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ከኢትዮጵያ ጎን ለቆሙ ሰላም ወዳጆች መሆኑን መገንዘብ የግድ ይላል።፡

ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር፣ ሰላም አየር መተንፈስ ጀምሯል ማለት ሁሉም አብቅቷል ማለት አይደለም። በተለይም በሰላም እጦት የተከሰቱ ድቀቶች ፈፅሞ ሊዘነጉ አይገባም። ሰላም ለማስፈን የተደረገው ጥረት በተለይም በጦርነት የተጎዱትን መልሶ በማቋቋምና በመደገፍ ሊደገም ይገባል። አስፈላጊውን የገንዘብና ሌሎችም ድጋፍ በማሰባሰብ ረገድ የአፍሪካ ህብረትም ሆነ ሌሎች በመሪነት ሊፈፅሙት ይገባል።

አሁንም ቢሆን ወቅቱ የኢትዮጵያን ችግሮች የመሸሽ ሳይሆን የማሸሽ ተጋድሎን ይጠይቃል።ኢትዮጵያን ነገ ማሳመር የሚችሉት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው። እድገቷም ውድቀቷም በልጆቿ እጅ ላይ ያረፈ ነው። በኢትዮጵያ ምድር የሰላም አየር መንፈሱ እንዲቀጥል እንደ ትናንቱ ሁሉ ነገም በኢትዮጵያ የመጣ በሰብዕናችን እንደመጣ፣እርሷን የነካ አይናችንን እንደነካ በመቁጠር አስተማማኝ ምርኩዝ መሆናችንን ልንቀጥል ይገባል። ኢትዮጵያ ካለ እኔና እናንተ አትበረታም።

በኢትዮጵያ ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የጦርነት ምዕራፍ እንዲዘጋ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከዳር እስከ ዳር በአንድነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ሌሎች የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች፣ ኢትዮጵያ ከግጭት የፀዳች አገር እንድትሆን ቁርጠኝነታቸውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

በአንድ አፍ ስለሰላም እየዘመሩ በሌላ አፍ ጦርነትን የሚደግፉ የፖለቲካ ተዋንያንም ሆኑ አክቲቪስቶች፣የሰላም መንገዱ እንዲዘጋና ጦርነቱ እንዲያገረሽ ከሚያደርጉ ፕሮፓጋንዳዎች እንዲታቀቡ ማድረግ መቼም መዘንጋት አይኖርበትም።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የኩታ ገጠም እርሻው እምርታ

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

ግብርናውን ከእጅ ወደ አፍ ግብርና ወደ ኮሜርሻል ግብርና ለማሸጋገር፣ ከበሬ ጫንቃ በማውረድ ሜካናይዝድ ለማድረግ መሥራት ከተጀመረ አመታት ተቆጥረዋል። ለእዚህም በቅድሚያ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች እጅ ያለውን ማሳ ወደ ኩታ ገጠም ሰፋፊ ማሳ ለመለወጥ እየተሠራ ነው።

በቀድሞው የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በአሁኑ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በኩል እየተከናወነ በቆየው በዚህ ግብርናውን የማዘመን ሥራም ኩታ ገጠም እርሻ (ኮሜርሻል ክላስተር) እየተስፋፋ መጥቷል። ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የተገኘ መረጃ እንደሚጠቁመው፣ ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ቤተሰቦችን በኩታ ገጠም ግብርና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረቡትን የ2015 በጀት አመት የስድስት ወራት ሪፖርት ተከትሎ ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንዳሉትም፣ በአሁኑ ወቅት የኩታ ገጠም እርሻ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ደርሷል። ይህም በጣም ተስፋ ሰጪ ውጤት መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ ገና ብዙ እንደሚቀርም ነው ያስገነዘቡት። «የዚህን እጥፍ ማድግ ብንችል በምርታማነት ላይም ከፍተኛ ለውጥ ይመጣል» ሲሉ አስታውቀዋል።

የግብርና ሚነስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ በቅርቡ ለኢቢሲ ሲገልጹ፤ «ግብርናችንን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የግብርና አመራረት ስልተ ምርት ወደ ኮሜርሻል ግብርና እንዲሻገር የማድረጊያው አንዱ መንገድ ኩታ ገጠም እርሻን ማስፋፋት ነው» ብለዋል። ኩታ ገጠም እርሻ በተለይ ባለፉት አራት አመታት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩንም ነው ያስታወቁት።

በዚህ በኩል የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ተልዕኮው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማምጣት፣ እንዲሞከሩ ማድረግ ከዚያም ለግብርና ሥርዓቱ ማስረከብ መሆኑን ይናገራሉ። ኢንስቲትዩቱ ኩታ ገጠምን ለማስፋፋት ከዚያ ቀደም ብሎም ሞክሯል፤ የማስፋት ሂደቱ ግን በጣም በጣም ውስን ነበር ሲሉ ገልጸው፣ በአገሪቱ ከአራት አመት በፊት ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር ያልበለጠ የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር እንደነበር አስታውሰዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ በለውጡ አመራር ለግብርና በተሰጠው ትኩረት አንዱ የሰፋው ግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ነው። በእነዚህ አራት አመታት የኮሜርሻል ክላስተሩ ብዛት ከአንድ ሚሊዮን ወደ ስድስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ደርሷል። በእነዚህ አመታት ከእጅ ወደ አፍ ግብርና ወደ ገበያ ተኮር ግብርና የመሸጋገሩ ሁኔታ በጣም ፈጣን ነበር።

አሁን በኢትዮጵያ ከሚታረሰው መሬት 45 በመቶው በግብርና ኮሜርሻል ክላስተር እየታረሰ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ይህ በጣም ትልቅ እምርታ እንደሆነም ነው ያሉት ያስታወቁት። በኩታ ገጠም እርሻ አርሶ አደር አንድ ላይ ሲሆን ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ምክር በመስጠት፣ ትርፍ ምርት በማግኘት በኩልም ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ መሬት ክላስተር ከተደረገ ቀጥሎ የሚመጣው ይህንን ሜካናይዝድ ማድረግ ነው። ለዚህም መንግሥት ባለፉት አራት አመታት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል። ለግብርናው ኮሜርሻላይዜሽን የሚያስፈልጉ ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ የሜካናይዜሽንና የመስኖ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ አድርጓል፤ አርሶ አደሩ ቆጥቦ ከሃያ እስከ አርባ በመቶ ቆጥቦ እነዚህን የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች (ትራክተሮች ኮምባይነሮች፣ የውሃ መሳቢያ ማሽኖች) በብድር እንዲወሰድ ተደርጓል።

ሊዝ ፋይናንስ አቅርቦት ለግብርናው ዘርፍ እንዲቀርብ በማድረግ ወደ ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በትራክተርና በሌሎች የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች እንዲታረስ መደረጉንም ጠቅሰው፣ በዚህም ሜካናይዜሽን 22 በመቶ፣ ኮሜርሻል ክላስተር ደግሞ 45 በመቶ ደርሷል ይላሉ። አሁንም ለሜካናይዜሽን ሊውል የሚችል የተዘጋጀ መሬት እንዳለ ጠቁመዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ወርቃለማሁ ጣሰው በሀዋሳ



ባለፉት አራት ዓመታት የኩታ ገጠም እርሻን ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር ወደ ስድስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ማሳደግ ተችሏል

ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ መምህር ናቸው። ፒኤችዲያቸውን በአግሪካልቸራል ኢኮኖሚ እያጠናቀቁ ይገኛሉ። በግብርናው ዘርፍ በገጠር ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ላይም ሠርተዋል፤ ረዳት ፕሮፌሰሩ የኢትዮጵያ ግብርና የሚታወቀው የተበጣጠሰ እርሻ (ፍራግመንትድ) በሚለው ነው ይላሉ።

«በአርሶ አደር ደረጃ ያለው መሬት አነስተኛ ነው፤ አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የእኛ ገበሬ የእቅድ ችግርም አለበት። የሚያቅደው የልጆቹን የምግብ ፍላጎት ማሟላት ላይ ተመስርቶ ነው። ከጓሮው እሸቱንም ሁሉንም ነገር ራሱ አሟልቶ ኑሮውን ማሸነፍ ይፈልጋል። ይህን ማድረግ ሲያስብ ካለው መሬት ግማሹን ለበቆሎ፣ ግማሹን ለስንዴ አድርጎ ማሳውን ይበጣጥሳል። በዚህ የተነሳ በአገሪቱ ሰፋፊ እርሻ ሳይታይ ቆይቷል ሲሉ ያብራራሉ።

በቀደመው ዘመን በባሌና በአርሲ የሜካናይዜሽን ሙከራዎች እንዲሁም የመንግሥት እርሻም እንደነበር አስታውሰው፣ በተለይ የመንግሥት እርሻው አወቃቀሩ ጤናማ ስላልነበረ በተለያዩ ሞዳሊቲዎች አርሶ አደሩን ወደ ሜካናይዜሽን ለማስገባት ጥረቶች ሲደረጉ መቆየታቸውን አመልክተዋል። ከዚያም ውጪ አርሶ አደሩ በራሱ እንዲሁም ባለሀብቶች አርሲና ባሌ ላይ ኮምባይነር ማሽነሪዎች ሥራ ላይ ማዋላቸውን ይጠቅሳሉ። ባለሀብቶቹ ለአርሶ አደሩ የኪራይ አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ገበሬውም እየተከራየ ሜካናይዜሽን ለመተግበር ጥረት ያደርጋል ይላሉ።

መንግሥት ይህን ሥራ ማስፋት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በፖሊሲ መምጣቱ በጣም ጥሩ ሀሳብ መሆኑን ጠቅሰው፣ የተበጣጠሰ ማሳ ተግዳሮት ሆኖበት ለቆየው የሰፋፊ እርሻ ሥራ አንዱ መፍትሄ ይኸው የኩታ ገጠም እርሻ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

የግብርና ሜካናይዜሽን ሲታሰብ አንዱ አብሮ የሚታሰበው ጉዳይ አርሶ አደሩ ከቤተሰብ ፍጆታ ያለፈ የቢዝነስ ሀሳብ እንዲኖረው ማድረግ ነው የሚሉት አግሮ ኢኮኖሚስቱ፣ የኮሜርሻል ክላስተር ዋና ፋይዳ የግብርና ትራንስፎርሜሽን መሆኑን ይጠቁማሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ትራንስፎርም የሚደረገውም ከፍጆታ ወደ ገበያ (ኮሜርሻላይዜሽን) ነው። የትልልቅ አገሮችም አመጣጥ ይኸው ነው፤ ግብርናው ቢዝነስ ይሆናል። አርሶ አደሩ ከጠነከረ ባለሀብት ይሆናል፤ ካልጠነከረም ሌላ ባለሀብት ግብርና ውስጥ ገብቶ አግሪካልቸራል ኮሜርሻላይዜሽን ይመጣል። በትራንስፎርሜሽን ውስጥ የአመለካከት፣ የእውቀት፣ የሀብት፣ የቴክኖሎጂ፣ የብዙ ነገሮች ጥያቄዎች አብረውት አሉ።

«ይህም ደረጃ በደረጃ የሚፈጸም ነው፤ ሥርዓት አለው፤ አንድ ጊዜ ሁሉንም ላድርግ ካልክ ይገለበጥብሃል፤ ምንም ነገር ላታደርግ ትችላለህ፤ ስለዚህ አላማው ግብርናን ደረጃ በደረጃ ወደ ኮሜርሻል ግብርና መቀየር ነው ሲሉ ያብራራሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንዳሉት፤ ግብርናው ወደ ኮሜርሻል ሲሄድ ዛሬ ብዙ ሕዝብ የያዘው ግብርና በጥቂት ሰዎች ብቻ ይካሄዳል፤ አብዛኛው ሰው ወደ ሚቀጥለው ዘርፍ (ኢንዱስትሪ) ይሄዳል። በዚህም የግብርናው ምርት ወደ ሌላ መልክ ሲቀየር ኢንዱስትሪ ነው አብሮ የሚመጣው። የዱቄት፣ የዳቦ፣ የዘይት፣ የኬክ ኢንዱስትሪ እያሉ አግሮፕሮሰሲንግ እንዱስትሪዎች ይቋቋማሉ።

ከግብርና የሚወጣው የሰው ኃይል ወደ ኢንዱስትሪው እየሄደ ግብርና ለቢዝነስ ነፃ እየሆነ ይመጣና በጥቂት ባለሀብቶች ከፍተኛ ምርት የሚመረትበት ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህም ምርታማነቱም ውጤታማነቱም በዚያው ልክ እየጨመረ ግብርናው ሳይንቲፊክ እየሆነ ይመጣል ሲሉ ይጠቁማሉ።

አርሶ አደሮች በክላስተር ማረስ መቻላቸው ትላልቅ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችን ለመጠቀም እንደሚያስችላቸውም ረዳት ፕሮፌሰር ወርቅአለማሁ ጠቅሰው፣ ሜካናይዜሽኑም ክላስተሩም የተሰወኑ ችግሮችን እንደሚቀርፉ ይናገራሉ። ኩታ ገጠም እርሻ ማንም ሰው ሊደግፈው የሚገባ ሀሳብ ነው፤ እንዴት ነው የሚተገበረው፣ ውጤታማ ነው ወይ ዘላቂ (ሰስቴይንአበል) ነው ወይ የሚለው ግን ሊሠራበት ይገባል ሲሉም ያስገነዝባሉ።

ግብርናን እንደ ቢዝነስ ብንወስደው አንድ ቢዝነስ ሊያድግ፣ ዘላቂ ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ ሲችል መሆኑንም አግሮ ኢኮኖሚስቱ ይጠቁማሉ፤ ሁልጊዜ ተሰጥቶት፣ በዘመቻ እየተከናወነ፣ በግፊት መቀጠል እንደሌለበትም ያሳስባሉ። አርሶ አደሩ ተጠቃሚ መሆኑን እየተረዳ ወደ ክላስተር ሥርዓቱ በፈቃደኝነት ገብቶ፣ ሕግ ኖሮት፣ የጥቅም ግጭት የሚፈታበት አሠራር እንዲኖር ከተደረገ፣ አርሶ አደሩም አዋጭነቱን ካረጋገጠ ቀጣይነት ይኖረዋል፤ በራሱ የሚሄድም ይሆናል ብዬ አስባለሁ ሲሉ ይጠቁማሉ።

አሁን በመንግሥት በኩል ማሽነሪ ማቅረብ፣ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ኤክስቴንሽኑ ላይ መሥራትን የመሳሰሉ ድጋፎች ያሉ ይመስለኛል። ይህን ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ያሉት አግሮ ኢኮኖሚስቱ፣ ከዚህ ይልቅ ለእኔ የሚመስለኝ፣ በሕግ መደገፍ ነው ይላሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ ማሽነሪ ከሚያስገቡ አስመጪና ላኪዎች ጋር አስተሳስሮ ተመጣጣኝ (ፌይር) በሆነ ዋጋ ገበሬውም ነጋዴውም ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሥርዓት መዘርጋት ይገባል። ቢዝነስ ሁልጊዜ ሰንሰለት አለው፤ አንዱ ጋ የሚቆም አይደለም፤ አምራቾች አሉ፤ ግብአት ይፈልጋሉ፤ ለምርቱ የግብይት ሥርዓት አለ፤ እነዚህ ሥርዓቶች ጠንካራ መሆን አለባቸው ሲሉም ይመክራሉ። በግብአት፣ በማሽነሪ አቅርቦትም ሆነ መለዋወጫ በማቅረብ በኩል ጠንካራ ሆኖ መገኘት እንደሚገባም ያሳስባሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ዛሬ የገባ ማሽነሪ ነገ ሊበላሽ ይችላል። መለዋወጫ ያስፈልጋል፤ መለዋወጫው ሁሌም ገበያ ላይ መገኘት ይኖርበታል፤ መለዋወጫ እየጠፋ የሚቆሙ ማሽነሪዎች እየታዩ ናቸው፤ ይህ ችግር ሊፈታ የሚችለው የገበያ ሥርዓቱ ሲመሠረት ነው፤ መለዋወጫው በአገር ውስጥ በግል ተቋም መመረት አለበት፤ ጋራዦች በቅርብ መኖር አለባቸው፤ የሚያንቀሳቅሱትም እውቀቱና ክህሎቱ ሊኖራቸው ይገባል።

ሥራው ጅምር ላይ ስለሆነ መንግሥት ለማበረታታት ሲል ብዙ ነገር እየሸፈነ ይሆናል። ቀስ በቀስ ግን ብዙውን ሥራ ለግሉ ዘርፍ እየተወ መንግሥት እጁን ማውጣት አለበት የሚል እምነት አለኝ ይላሉ። መንግሥት ድጋፍ በማድረግ ይህን ጉዳይ ሊወጣው እንደማይችልም ጠቁመው፣ እሱ ስታብሊሽ ማድረግ እና ሲስተም ላይ ማተኮር እንዳለበት ይመክራሉ። ሁሉም ለጥቅሙ ሲል ቢዝነስ ሥርዓት ውስጥ ይገባል፤ ከዚያም ራሱን እየቻለ ይሄዳል ነው የሚሉት።

ድጎማ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉም አግሮ ኢኮኖሚስቱ አቶ ወርቃለማሁ ይጠቁማሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን የግብርና ምርቶች ይደጎማሉ። የምርቱ ዋጋ ወጪያቸውን የማይሸፍን ከሆነ፣ የማምረቻ ዋጋው በጣም ከፍተኛ ሆኖ ከተገኘ መንግሥት ፖሊሲ ቀርጾ ድጎማ ሊያደርግ ይችላል ሲሉ ገልጸው፣ የመንግሥት ድጋፍ በባለሙያ፣ በቴክኒክ፣ ጋራዦችን በማቋቋም የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የኤክስቴንሽን ሠራተኞች ክትትል እንዲያደርጉ በማድረግ ላይ ማተኮር እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

ሜካናይዜሽን አሉታዊ ጎን እንዳለውም አግሮ ኢኮኖሚስቱ ያስገነዝባሉ። እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ «ሜካናይዜሽን ካፒታል ኢንቴንሲቭ ነው፤ በእኛ አገር ከፍተኛ የሰው ኃይል አለ፤ አገሪቱ ውስጥ ካለው ሥራ አብዛኛው ያለው ገጠር ነው፤ ግብርናው ካፒታል ኢንቱሲቭ ከሆነ አንድን ኮምባይነር ሁለትና ሦስት ሰዎች ያንቀሳቅሱታል፤ በጣም ብዙ ሰው የሚውልበትን እርሻ እሱ በጥቂት ሰዎች ይሠራዋል፤ ይህ ሁኔታ የሥራ አጥ ቁጥርን ሊጨምር እንደሚችል መታሰብ ይኖርበታል።

ከግብርናው ዘርፍ ሥራ እያጣ የሚመጣው ኃይል ሌላ ሥራ ውስጥ እንዲገባ መደረግ እንደሚኖርበትም ጠቅሰው፣ ለእዚህ መፍትሄው አግሮ ፕሮሰሲንግ እኩል አብሮ እንዲሄድ ማድረግ መሆኑን ያመለክታሉ። የግብርና ምርቶች አግሮ ኢንዱስትሪዎች ገብተው ፕሮሰስ ሲደርጉ ብዙ የሰው ኃይል እንደሚፈልጉም ነው የጠቆሙት።

ማሽነሪ፣ መለዋወጫ፣ ነዳጅ ከውጭ ነው የሚመጣው፤ አገራችን የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛ እጥረት አለባት ሲሉ ጠቅሰው፣ ትክክለኛው ወጪና ገቢ ተሰልቶ ቢዝነሱ በራሱ አዋጭ ነው ወይ የሚለው በጥናት መመለስ እንዳለበትም ይጠቁማሉ። እኔ አግሪካልቸራል ሜካናይዜሽን ባክግራውንዱ አለኝ እውቀቱ አለኝ። በግብርና ቴክኖሎጂ ላይ ከመልካስ ግብርና ጋር ሠርቻለሁ የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ ከውጭ የሚገቡ አንዳንድ ማሽነሪዎችና መለዋወጫዎችም በአገር ውስጥ የሚመረቱበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፤ ይህን የሚደግፈውን የኢንዱስትሪውን ክፍል የሚያጠናክር ተቋምም ያስፈልጋል ሲሉ ያሳስባሉ።


ረዳት ፕሮፌሰሩ ኮሜርሻል እርሻ ለኢትዮጵያ እድገት ተስፋ አለው ብለው እንደሚያምኑ ጠቅሰው፣ ኅብረተሰቡ እንዲቀበለው ተደርጎ ማስለመድ ማስፋፋት ላይ መሥራት እንደሚገባ ይጠቁማሉ። ክላስተሩ አፈጻጸም ይጨምራል፤ በኮምባይነር ስትሰበስብና ስትወቃ በእጅ ስትሰበሰብና ስታወቃ ልዩነት አለው፤ ክላስተሩ የድህረ ምርት ብክነትን ይቀንሳል፤ ምርታማነትን ይጨምራል፤ አርሶ አደሮቹ በማህበር ስለሚሠሩ በግዥና ሽያጭ ወቅት የመደራደር አቅማቸውንም ይጨምራል፤ በዚህም የተሻለ ዋጋና ገበያ የማግኘት ዕድል ይፈጥርላቸዋል ሲሉ አብራርተው፣ ሥራው ግን ማኔጅመንት ይጠይቃል፤ ቴክኒካሊ በባለሙያ መደገፍ አለበት ብዬ አስባለሁ ሲሉም ያስገነዝባሉ።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ምቹ የትምህርት ቤት መጸዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**





ከአካል ጉዳተኞች መብት ጋር በተያያዘ በርካታ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ ወደ ሁሉም አዕምሮ የሚመጡ ሃሳቦችም ቀላል አይደሉም፡፡ ከሁሉም ሃሳቦች ቀድሞ ወደአዕምሮ የሚመጣው ግን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምቹነት ነው፡፡ ከነዚሁ ተቋማት መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ደግሞ ትምህርት ቤት ነው፡፡

አካል ጉዳተኝነት በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ድንገት በሚደርስ አደጋ በሁሉም ሰው ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡ በተለያየ ምክንያት የአካል ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች ምቹ አገልግሎት የማግኘት መብት ቢኖራቸውም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ የሚገኙ አገራት ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም የትምህርት ተቋማት ከመጸዳጃ ቤት እስከ መማሪያ ክፍል ድረስ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር ረገድ ብዙ ርቀት አልተጓዙም፡፡

ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች ከሌሎች ተማሪዎች እኩል መስተናገድ እንዲችሉ ተደርገው መገንባት ያለባቸው ቢሆንም በገሃድ የሚታየው ሁኔታ ተቃራኒ ነው፡፡

አካል ጉዳት የራሱ የሆነ ግልጋሎትን ይፈልጋል፡፡ መሰረታዊ የሚባሉ ፍላጎቶችም አሉት፡፡ እናም በትምህርት ተቋማትም እነዚህ ነገሮች ካልተሟሉ የችግሩ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች በቀላሉ መማር አይችሉም፡፡ በዚህም አካል ጉዳተኞች ዛሬም ድረስ እየተጎዱ ይገኛሉ፡፡ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽና አመቺ ትምህርት ቤቶች ባለመገንባታቸው ብዙዎች ከትምህርት ገበታ ውጪ ለመሆን ተገደዋል፤ ለተደራራቢ ችግርም ተዳርገዋል፡፡ በትምህርት ቤቶች የመጸዳጃ ቤት ጉዳይ እንኳን ለአብነት ቢነሳ እጅግ ውስብስብ ችግሮች አሉበት፡፡ በአብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መጸዳጃ ቤቶች አይደለም ለአካል ጉዳተኞች ሙሉ አካል ላላቸውም ምቹ አይደሉም፡፡

መፀዳጃ ቤቶች ከጽዳት አንስቶ ለአካል ጉዳተኞች ምቹና ደህንነታቸው የተጠበቀ አይደሉም፡፡ አንዳንድ አካል ጉዳተኞች ችግሩን ተቋቁመው ወደ መፀዳጃ ክፍሎች ውስጥ ገብተው ለመጠቀም ሲጣጣሩ የመፀዳጃ ክፍሎቹ ብልሹና አመቺ ባለመሆናቸው «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ ተንሸራተው ወድቀው ለተጨማሪ የአካል ጉዳት ሲዳረጉ ይስተዋላል፡፡ በተለይ ለአይነ ስውራንና በተሽከርካሪ ወንበር እንዲሁም ክራንች ለሚጠቀሙ አካል ጉዳተኞች ሁኔታው የከፋ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የተለያዩ ሕጎችን በአዋጅ ደረጃ አውጥታለች፡፡ ከዚህ ውስጥ አንዱ የሕንፃ ግንባታ ህግ ሲሆን ህጉ አዋጅ 624/2001 ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ አዋጅ በአንቀጽ 36 መሰረት ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ሲገነቡ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

ውስጣቸው በተሽከርካሪ ወንበር ለመንቀሳቀስ ወይም ለመራመድ የሚያስችሉ ሆነው መገንባት እንደሚኖርባቸውም ይጠቅሳል፡፡ በህንፃ ደረጃ መውጣት ለማይችሉ አካል ጉዳተኞችም ለመንቀሳቀስና ወደሚፈልጉበት ቦታ ለመድረስ የሚያስችላቸው መወጣጫ ማካተት እንዳለበትም አዋጁ ያስቀምጣል፡፡ የመጸዳጃ ቤቶችም ቢሆኑ ለአካል ጉዳተኞች አመቺ በሆነ መልኩ መሰራት እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡

ሆኖም የሕንፃ ግንባታውን ዲዛይን ከሚያደርጉ ሰዎች ጀምሮ እስከ ሕንፃ ባለቤቶች ድረስ ህጉን ተግባራዊ ሲያደርጉ አይታዩም። የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም የማስፈጸም አቅማቸው ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ አካል ጉዳተኞችን ትልቅ ዋጋ እያስከፈላቸው ይገኛል፡፡ ተማሪ አካል ጉዳተኞችም በዚሁ ችግር ምክንያት በቤታቸው እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል፡፡

ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የተለያዩ ጥናቶች በአለማቀፍ ደረጃ ተሰርተዋል፡፡ ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስነ-ህዝብ ፈንድ እና የስነ-ህዝብ ካውንስል የተሰራ የአንድ ጥናት ሪፖርት እንዳስቀመጠው፤ የአካል ጉድለት ካለባቸው ሶስት ልጃገረዶች አንዷ በቤትና በማህበረሰብ ውስጥ ስልታዊ እና የኃይል ጥቃት ይደርስባታል፤ እንግልት ይገጥማታል። በትምህርትና በስራ ቅጥርም እንዲሁ ተጨማሪ የከፉ ችግሮች ያጋጥሟታል፡፡ ለዚህ ደግሞ መንስኤው በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ትምህርት ቤት አለመሄዳቸውና አለመማራቸው እንደሆነ ጥናቱ ያስቀምጣል፡፡

እ.ኤ.አ በ2002/2003 በስነ-ህዝብ ካውንስል የወጣት አዋቂዎች የዳሰሳ ጥናት መሰረት ደግሞ፤ የአካል ጉድለት ከሌለባቸው 48 በመቶ ልጃገረዶችና 55 በመቶ ወንድ ልጆች ጋር ሲነፃፀሩ በትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩት የአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች 23 በመቶ ናቸው። ለዚህ ሁኔታ መፈጠር መንስኤው ደግሞ አመቺ የመጸዳጃ ቤት ማግኘት አለመቻል ነው ይላል ጥናቱ፡፡

እንደጥናቱ ከሆነ አካል ጉዳተኞች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚደርስባቸው መንገላታት የተነሳ ወላጆች ሳይቀሩ ከትምህርት ቤት እንዲቀሩ ያስገድዷቸዋል፡፡ ልጆቻቸው ከቤት ከወጡ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች እና እንግልት ይደርስባቸዋል ብለው ይጨነቃሉ፡፡ በተለይ ኢትዮጵያን ጨምሮ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ያሉ ልጃገረዶች የሚቸገሩት በትምህርት ቤቶች ውስጥ በቂ ውሃ እና መፀዳጃ ቤት ባለመሟላቱ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ችግሩ ለአቅመ-ሔዋን በደረሱ ልጃገረዶች ላይ እንደሚያይል ነው ጥናቱ የሚያሳየው፡፡ አካል ጉዳተኞች ከትምህርት የመቅረታቸው ምስጢርም በዋናነት ከዚሁ ጋር ይያያዛል፡፡

በየትምህርት ቤትም ይኸው ችግር ጎልቶ ይታያል፡፡ በችግሩ ደግሞ ሴቶቹ እጅጉን ይሰቃያሉ፡፡ የአካል ጉዳተኛ ሴቶች ባህሉም ይዟቸው ተፈጥሮም ሆኖባቸው እንደሌሎች ሴቶች እንደልባቸው አይጠቀሙም፡፡ ባህሉ ሸሸግ፤ ሸፈን ብለው እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል፡፡ ተፈጥሮ ደግሞ ከወር አበባ ጀምሮ በተደጋጋሚ ንፅህናዋን እንድትጠብቅ ያስገድዳታል፡፡ በዚህ ምክንያት መጸዳጃ ቤት በተለይ ለአካል ጉዳተኛ ሴቶች መሰረታዊና አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና የአብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ይህንን ሲያሟሉ አይታይም፡፡ ከትምህርት ቤት ጋር ባይገናኝም የአካል ጉዳተኞችን የመጸዳጃ ቤት ችግር በስፋት ያሳያልና በአንድ ወቅት የሆነውን ታሪክ እናንሳ፡፡

አይነ ስውር ናት፡፡ በሆዷ ፅንስ አለ፡፡ የመውለጃ ቀኗ እየደረሰ ነው፡፡ ምጧ ከመጣ ለመውለድ ያሰበችው በደቡብ ክልል ጌዲኦ ዞን ዲላ ዙሪያ ወረዳ በሚገኘው ጨጨ ጤና ጣቢያ ውስጥ ነው፡፡ የተፈጥሮ ህግ ነውና ምጧ መጥቶ ለመውለድ ወደዚሁ ጤና ጣቢያ አመራች፡፡ ጤና ጣቢያ ስትደርስ ግን ሀኪሞች ወደ ማዋለጃ ክፍል ሳይሆን መፀዳጃ ቤት አስገቧት፡፡ እርሷ አታይምና ይህን አላስተዋለችም፡፡ ነገር ግን ደግሞ የመፀዳጃ ቤቱ ጠረን በብርቱ ፈትኗታል፡፡ ከምጡ አይብስምና ችላው እዛው ቆየች፡፡ ቦታው እንኳን ለአይነስውር ነብሰ ጡር ይቅርና ሙሉ አካል ላለውም ሰው ምቹ አልነበረም፡፡ አይነ ስውሯ ሴት ማዋለጃ ክፍል ገብታ ልጇን እስክትገላገል ድረስ ሁሉን ችላ በስቃይ በመፀዳጃ ቤቱ ውስጥ ቆይታለች፡፡ ጉዳዩ መገናኛ ብዙሃን ጆሮ ደርሶ ድብልቅልቁ ወጣ እንጂ ልክ እንደርሷ ጥቂት የማይባሉ አይነስውራን ነብሰ ጡር ሴቶች ተፈትነው እንደነበር መገመቱ አያዳግትም፡፡

ለዚች አይነ ስውር ነብሰ ጡር ሴት የደረሰላትና ከችግሯ ያወጣት ማንም ሰው የለም፡፡ ሁሉም ነገር ከሰው ጆሮ የደረሰው በፈተና ውስጥ ካለፈች በኋላ ነው፡፡ ለዚህም ነው የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ መታሰብ ያለበት ሕጉን ከማክበር ጀምሮ ነው የሚባለው፡፡ ምክንያቱም ሕግ ሲከበር መሰረት ይጣላል፤ ተገልጋዩም ፍላጎቱን እያሟላ ይሄዳል፡፡

ታዲያ ይህ ጉዳይ እንዴት ትኩረት ያግኝ ፤ እንዴትስ ወደ ስራ ይገባበት ከተባለ መልሱ ቀላል ነው፡፡ አካል ጉዳተኝነት ሁሉም ሰው ሊገጥመው የሚችል ችግር ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ኃላፊነት እንዳለበት አምኖ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚያ ባሻገር ደግሞ ሕጉን የሚተገብሩና ለአካል ጉዳተኞች ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ ተቋማትን ማጉላት ያስፈልጋል፡፡ ለሌሎች ተሞክሯቸውን የሚያካፍሉበትን እድል መፍጠርም ይገባል፡፡

በዚህ ረገድ ለሌሎች ምሳሌ ከሚሆኑ ትምህርት ቤቶች አንዱ ደጅ አዝማች ወንድይራድ አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት በከተማ ግብርና፣ አረንጓዴ ልማት፣ የተቀናጀ ፅዳትና ውበት እንዲሁም የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ባለው የመጸዳጃ ቤት አገልግሎቱ ንጽህና ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ ሽልማት አግኝቷል፡፡

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ሰለሞን ክቤ እንደሚናገሩት፤ የትምህርት ጥራትን ከሚያረጋግጡ መሰረታዊ ነገሮች አንዱ የትምህርትቤት ምቹነት ነው፡፡ በዚህም ሁሉም ተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ ከማድረግ አኳያ በትምህርት ቤቱ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ደግሞ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ነው፡፡

«ፍትሀዊነትም አንዱ የትምህርት ጥራት ፓኬጅ በመሆኑ በትምህርት ቤት ማሻሻያ ሥራችን አማካይ በሆነ ቦታ ላይ አካል ጉዳተኞች የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ የማስቻል ሥራ ተከናውኗል» ሲሉ ርዕሰ መምህሩ ይናገራሉ፡፡ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት ተደራሽነትን በፍትሀዊነት ከማረጋገጥ አኳያም የልዩ ፍላጎት አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው ተብለው የተለዩት 483 ተጠቃሚ የሚያደርግ 64 ዘመናዊ መጸዳጃ ቤቶችን ማዘጋጀት ችሏል፡፡ መጸዳጃ ቤቱ የተሰራውም እንደ አካል ጉዳታቸው ሁኔታ እንዲጠቀሙ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር ትምህርት ቤቱ የልዩ ፍላጎት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ፊዚዮ ቴራፒ ማዕከል አለው፡፡ በዚህ ማዕከል ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ በአካቶ ትምህርት እንዲደገፉ ይሆናል፡፡ ማእከሉ ባለሶስት ወለል 36 የመማሪያ ክፍሎች ያሉት ሲሆን፤ ሦስቱም ወለል ላይ ዘመናዊ መጸዳጃ ቤቶች ተሟልተውለታል፡፡ በተጨማሪም ሕንጻው ላይ ሲወጡ ሙሉ ራንፕ ስላለው የአካል ጉዳተኞች አይቸገሩም፡፡ መለስተኛ የሕክምና መስጪያ ማዕከላት፣ ማረፊያ ክፍሎች፣ ማሰልጠኛ ክፍሎች፣ የመማክርት ክፍሎች፣ የክላስተር ሴንተሮችና ሪሶርስ ሴንተር አሉት፡፡

እንደ ርእሰ መምህሩ ገለፃ፣ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት አለመኖሩ የመማር ማስተማር ሥራውን በብዙ መልኩ ፈትኖት ነበር፡፡ ተማሪዎቹ በስነልቦናም ሆነ በትምህርታቸው ጫና እንዲያርፍባቸው አድርጓቸዋል፡፡ ለዚህም ማሳያው በ2009 ዓ.ም በተሰራው የዳሰሳ ጥናት መሰረት መጠነ ማቋረጡ መጨመሩ ነው፡፡ በዚህም ከትምህርት ቤት እስከመቅረት የደረሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የመጠነ ማቋጥ መጨመር ምክንያትም ይኸው በአካባቢው ላይ ያሉ አካልጉዳተኛ ተማሪዎች ቁጥር መጨመርና ለእነርሱ የሚመጥን የመፀዳጃ ቤት አለመኖር ነበር፡፡

ሆኖመም ችግራቸው ከተፈታ ተማሪዎችን በፍላጎትም በእውቀትም ማገዝ እንደሚቻል መተማመን ላይ በመደረሱ ወደ ሥራ ተገብቶ ውጤቱ እጅግ አስደሳች ሆኗል፡፡ ለአብነትም የ2015 ዓ.ም ውጤታቸውን ሲታይ ካሉት 483 ተማሪዎች ውስጥ በክፍል ፈተና 50 እና ከዚያ በላይ ያመጡት 87 ነጥብ 8 በመቶ ናቸው፡፡

አገልግሎቱ የጀመረው ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት ቢሆንም ንጽህናው አሁን ጭምር የሚጠቀሙበት አይመስልም፡፡ ልክ እንደሆቴሎች ሁሉ በአማካይ በአንድ ሰዓት ልዩነት ይጸዳል፡፡ አካል ጉዳተኞችን ለመደገፍ ከስልጠና ባሻገር እንደ ተሽከርካሪ ወንበር አይነት መሳሪያዎችን በመስጠት ትምህርት ቤቱ ያግዛቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ጀምሮ የተለያዩ አካላት እገዛን አድርገዋል፡፡

ከሁሉ በላይ ግን የትምህርት ቤቱ አመራሮች ሥራ የላቀ ድርሻ አለው፡፡ ትምህርት ቤቱም ፕሮጀክት ቀርጾ ድጋፍ ሊያደርጉለት የሚችሉ አካላትን ከመጠየቅ ወደኋላ አይልም፡፡ ስለዚህም ሌሎች ትምህርት ቤቶችም ከእኛ ቢዎስዱ የሚሉት አጋዥ አካላትን ማፈላለግና በእገዛቸው ምን ምን ነገሮች እንደተሰሩ ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም የራሳቸውን ክፍት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ እነርሱ የተሻሉ ከሆኑ ለሌሎች መድረስ መቻል አለባቸው ሲሉ ርእሰ መምህሩ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ፡፡

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ የበዓል ፍላጎት ላይ ትኩረት በማድረግ የአቅርቦት ችግር እንዳይገጥም የተደረገው ጥረት ቀጣይነት እንዲኖረው ይሰራል››

-አቶ ሙላቱ ፅጌ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር



**ምህረት ሞገስ**

የአዲስ አበባን ነዋሪ እያማረረ ያለው የሸቀጦች የዋጋ ንረትን ችግር ለማቃለል የከተማ አስተዳደሩ እየሠራቸው ካሉ ሥራዎች መካከል አንደኛው በሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት በኩል ለህብረተሰቡ የተለያዩ ምርቶችን ማቅረብ ነው። በተለይ የበዓል ሰሞን የዋጋ ንረት የተለመደ በመሆኑ፤ የሸማች ማህበራቱ በዓላትን ተከትሎ የሚያጋጥመውን የዋጋ ንረት ለመከላከል ምን ያህል ሠሩ የሚሉ እና ሌሎችም ከሸማች ማህበራት አሠራር ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመያዝ ወደ አዲስ አበባ ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ በማምራት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ሙላቱ ፅጌን በማነጋገር እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን የፋሲካ እና የኢድ በዓል ተከብሯል። በእነዚህ በዓላት የከተማው ህዝብ በዋጋ ንረት እንዳይሰቃይ ምን ሠራችሁ ከሚለው እንጀምር።**

**አቶ ሙላቱ፡-** የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ በሥሩ ብዙ ዳይሬክቶሬቶች አሉት። የሚሠራቸውም ሥራዎች ሰፊ ናቸው። ለአብነት ማደራጀት እና አቅርቦት ላይ የሚሠሩ ሠፋፊ ሥራዎች አሉ። በዓል ሲመጣ ደግሞ የበዓል ፍላጎት ላይ ትኩረት በማድረግ በተቻለ መጠን የአቅርቦት ችግር እንዳይገጥም ትልቅ ጥረት ይደረጋል። ከሚመከታቸው አካላት ጋር በተለይም ከክልሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሰፋ ያለ ሥራ ይሠራል።

ሰሞኑንም በከተማችን የሚገኙ የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራትን ከአማራ ክልል እና ከኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ አምራች ዩኒየኖች ጋር በማገናኘት የምርት ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል። በዚህም ወደ ከተማችን በሰፊው ምርት ገብቷል። ለአብነት ጤፍ እና የስንዴ ዱቄትን መጥቀስ ይቻላል።

ከኢንዱስትሪ ምርቶች ጋር ተያይዞም የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። በተጨማሪ በበዓል በስፋት የሚፈለጉት የቁም ከብቶችም ለገበያ ለማቅረብ ትስስር በመፍጠር በስፋት ወደ ከተማ እንዲገቡ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል። ለምሳሌ አግሮ ሴፍት ከሚባለው የሼህ አላሙዲን ድርጅት ጋር በመቀናጀት በርካታ ለበዓል የሚሆን ሰንጋ ወደ ከተማው እንዲገባ ተደርጓል። ዶሮን በተመለከተም በተመሳሳይ መልኩ ከአምራች ተቋማት ጋር በመገናኘት ብዙ ሥራ ተሠርቷል።

እነዚህ ወደ ከተማ የገቡ ምርቶች ደግሞ የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት ባሏቸው ሱቆች እና በሁሉም ክፍለ ከተሞች ላይ የእሁድ ገበያ በተሰኙት መዳረሻዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እነሽንኩርት እና ሌሎችም ለበዓል የሚያስፈልጉ ምርቶችን ማቅረብ ተችሏል።

በተጨማሪ ከተለያዩ አካባቢዎች ምርት ያላቸው አምራቾች በራሳቸው ተሸከርካሪ ምርታቸውን ይዘው ወደ ከተማው እንዲገቡ እና እንዲሸጡ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በተለይ ማንኛውም የከተማው ነዋሪ ሊያስተውለው በሚችል መልኩ ዶሮ በየዋና ዋና መንገዶች ላይ ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ማድረግ ተችሏል። በዚህም ህዝቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገበያይ ማድረግ ተችሏል። በእነዚህ ሥራዎች የተሳካ ውጤት ተገኝቷል ማለት ይቻላል።

ይህ ያለቀለት አይደለም፤ ይቀጥላል። የእሁድ ገበያ ወደ ፊትም አይቋረጥም፤ ይቀጥላል። ከአምራች አርሶ አደሮች እና ከአምራች የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ጋር በመገናኘት ሸማቹን የመጥቀም ሥራ ይሠራል። እዚህ ላይ ለበዓል ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርባል ሲባል አንፃራዊ ነው። የምርቱ ዋጋ ሲጨምር የመሸጫ ዋጋውም ይጨምራል። ነገር ግን ከነጋዴው በእጅጉ የተሻለ ነው። ይህንን ማንም ማረጋገጥ ይችላል።

ከትንሹ ከስድስት ብር ጀምሮ እስከ ስድስት መቶ ብር ልዩነቶች አሉ። ከጤፍ ብንነሳ በኩንታል ሰፊ ልዩነት አለው። ሽንኩርት እና ድንች ላይም ነጋዴ ላይ ያለው ዋጋ እና ሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት ጋር ያለው ዋጋ ይለያያል። የእነዚህ ሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት ዓላማ አባሎቻቸውን ማገልገል ነው። ሁለተኛ ሥራቸው ደግሞ የከተማውን ነዋሪ መጥቀም ነው። ስለዚህ በጣም ጥቂት ወጪያቸውን የሚሸፍን ማለትም የተሸከርካሪ እና የጫኝ እና የአውራጅ ወጪያቸውን የሚሸፍን እንጂ ሌላ ትርፍ ይዘው አይሸጡም። ይህ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው ካፒታል ቢኖራቸውም በቂ ባለመሆኑ መንግስት የሕብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ችግራቸውን ለመፍታት አንድ ቢሊዮን ብር ለዩኒየኖች በተዘዋዋሪ ብድር መልክ መድቦላቸው እያንዳንዱ ዩኒየን 100 ሚሊዮን ብር አግኝቷል። በዚህም በሰፊው ምርትን በቀጥታ ከአምራች እየወሰዱ በተመጣጣኝ ዋጋ ለነዋሪው እንዲሸጡ ዕድል ተከፍቷል። በተጨማሪ አቅማቸውን የበለጠ ለማጠናከር መጋዘኖችን የሚሠሩበት ቦታ እንዲሰጣቸው የከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ አስተላልፏል። በሂደት ዋና ዋና ቦታዎች ላይ በቂ መጋዘኖችን ገንብተው ምርት በበቂ ሁኔታ ወደ ከተማው እየገባ የኑሮ ውድነቱን ለማስታገስ ታቅዶ እየተሠራ ነው።

እነዚህ ማህበራት የሚፈለገውን ዓላማ እንዲያሳኩ፤ በዚህ ዓመት በርካታ የሪፎርም ሥራዎች ተሠርተዋል። የአመራር ችግር ያለበት የአመራር ችግሩን እንዲፈታ፤ የሎጀስቲክ ችግር ያለባቸው የሎጀስቲክ ችግራቸውን እንዲፈቱ፤ በተመሳሳይ መልኩ የአደረጃጀት ችግር ያለባቸውም የአደረጃጀት ችግራቸውን እንዲፈቱ የመጋዘን ችግር ያለባቸውም የመጋዘን ችግራቸውን እንዲፈቱ ተሠርቷል። በቀጣይም በበዓል ብቻ ሳይሆን ከበዓል በኋላም 152 የሚሆኑ የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራትን እና 11 ዩኒየኖችን ይዘን በሰፊው እየሠራን የምንቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ 152 የሚሆኑ የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት አሉ። ነገር ግን ከህዝቡ ፍላጎት አንፃር የሸማች ማህበራት ብዛት እና አቅም እንዴት ይታያል?**

**አቶ ሙላቱ፡-** እነዚህ የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት በዋናነት የተደራጁት የአባሎቻቸውን ማህበራዊ ችግር ለመፍታት ነው። በተጨማሪ ግን ማህበራዊ ኃላፊነት ስላለባቸው ለነዋሪውም ጭምር የሚጠበቅባቸውን ሚና ይወጣሉ። ነገር ግን የከተማውን ነዋሪ ፍላጎት በህብረት ሥራ ማህበራት ብቻ እናሟላለን ማለት አይደለም። የራሳቸው ድርሻ አላቸው፤ በድርሻቸው ልክ ሚናቸውን ይወጣሉ። ባላቸው የመጨረሻ አቅም ልክ የድርሻቸውን ሚና ሲጫወቱ፤ በሌላ በኩል ነጋዴውም ሆነ አምራቾች እና የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ወደ ከተማዋ ምርት አስገብተው ለነዋሪው ያቀርባሉ።

በእሁድ ገበያዎች ላይ እንዳየነው አርሶ አደሩ ቀጥታ ምርቱን ለገበያ እያቀረበ ነው። በተለይ ትኩስ አትክልት ለነዋሪው እያቀረበ ይገኛል። ሁሉም የየራሱ ድርሻ አለው። ማህበራቱ ግን የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ቁመናቸው እንዲስተካከል እና አቅማቸው እንዲዳብር መንግስትም በጣም እያገዘ ነው። እነርሱም የውስጥ አቅማቸውን በማጠናከር ብቃት እንዲኖራቸው እየሠሩ ነው። አጫጭር ስልጠናዎችም እየተሰጡ ብቃታቸውም እየጨመረ ይገኛል። እስከ አሁን በአንድ ዓመት ውስጥ ወደ ሶስት መቶ 34 ሺህ ኩንታል እህል ወደ ከተማው ገብቷል። ይህ ቀላል አይደለም። እነዚህ በዋናነት መሠረታዊ የሚባሉት ምርቶች ናቸው። ጤፍ እና የስንዴ ዱቄት የመሳሰሉ መሰረታዊ ምርቶችን በማስገባት ገበያው እንዲረጋጋ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ማስገባት ብቻ ሳይሆን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህዝቡ ከማድረስ አኳያ እየተጫወቱት ያለው ሚና ቀላል አይደለም። ነገር ግን ይህ ማለት በውስጣቸው ችግር የለም ማለት አይደለም።

የሕብረት ሥራ ማህበራቱ እንደማንኛውም ተቋም የውስጥ የማኔጅመንት፣ የሎጀስቲክ፣ የትራንስፖርት እና የሠው ሃይል የመሳሰሉት ሌሎችም ችግሮች እንዳሉባቸው አይካድም። ያም ሆኖ እየደገፉ እንዲበቁ ከማድረግ አኳያ የሕብረት ስራ ኤጀንሲው በየዓመቱ እያቀደ ይሠራል። ቁመናቸውን ለማጠናከር አዋጁ በሚፈቅደው መሠረት ኦዲት እናደርጋቸዋለን። የህግ ክፍተታቸው በዚሁ ተቋም በኩል ድጋፍ እንዲያገኝ ይደረጋል። ይህ ሁሉ ብቁ ሆነው የበለጠ ድርሻቸውን እንዲወጡ ለማስቻል በማሰብ ነው። ይሁን እንጂ መዘንጋት የሌለበት የከተማውን ገበያ ድርሻ ሙሉ ለሙሉ ማህበራት ይሸፍናሉ ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት በእርግጥ የተለያዩ ምርቶችን ሲያስገቡ ቢታዩም ለህብረተሰቡ በብዛት አያከፋፈሉ አይደለም የሚሉ ተደጋጋሚ አቤቱታዎች ይቀርባሉ። እዛ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሙላቱ፡-** እውነት ነው፤ በተለይ መሠረታዊ ሸቀጥ የሚባሉ ዘይት እና ዱቄት እንዲሁም ስኳርን የመሳሰሉ ምርቶች ላይ ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ይቀርቡ ነበር። በእርግጥ አሁን ዱቄት ላይ ብዙ ትኩረት አይደረግም። እጥረትን በተመለከተ ችግሩ ያለው በአገር ደረጃ ነው። እርሱ ላይ የሚወስነው ንግድ ሚኒስቴር ነው። ንግድ ሚኒስቴር ለአዲስ አበባ የሰጠው ኮታ ደግሞ በአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በኩል ኮታው ይመጣል። ንግድ ቢሮ ደግሞ በሸማች ማህበራት በኩል እና በተመረጡ ነጋዴዎች ለህዝብ እንዲደርስ ይደረጋል። የፍላጎት እና የአቅርቦት ችግር የታወቀ ነው። የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ነው። ኮታው በፊት በነበረው የህዝብ ቁጥር ልክ ነው። በፊት የተሰሩ ኮታዎች በመሆናቸው በተወሰነ መልኩ ክለሳ ይፈልጋሉ። ኮታው አሁን በተጨባጭ ካለው የከተማው ነዋሪ ጋር የሚመጣጠን ባለመሆኑ በህዝቡ ፍላጎት መጠን እንዲቀርብ የሚመለከተው አካል እየሠራ ነው።

ከመጣውም ውስጥ ደግሞ የመጣው ሁሉ በትክክል በተመጣጣኝ ዋጋ ሕብረተሰቡ ጋር ይደርሳል ወይ? የሚለው ጥያቄ ትክክል ነው። እኛም በተጨባጭ አልፎ አልፎ የሥነምግባር ችግር ያለባቸው አጋጥመውናል። ይህ ምናልባት በግለሰብ ሊገለፅ ይችላል። ተቋም ብሎ ማጠቃለል ባይቻልም በባለሙያም ሆነ በአመራር ግለሰቦች ላይ ችግር ያጋጥማል። የሥነምግባር ችግር ሲያጋጥም ያለምንም ርህራሔ እርምጃ እየወሰድን ነው። ለምሳሌ ባለፈው ዓመት ብቻ 264 የሚሆኑ በአጠቃላይ እርምጃ የተወሰደባቸው አሉ። ይህ ከመሰረታዊ ሸቀጥ ጋር ብቻ የሚያያዝ አይደለም። ነገር ግን በሌሎችም ችግሮች ለምሳሌ ሒሳብ በማጉደል እና አቅርቦትን በተቀመጠው ህገ ደንብ መሠረት ለሸማች ባለማቅረብ እንዲሁም በአጠቃላይ ተገቢውን ሥራ ማከናወን ሲገባቸው ያላከናወኑ ከሆነ ተጠያቂ ይደረጋሉ።

ኤጀንሲው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራትን ኦዲት ያደርጋል። በየዓመቱ ኦዲት ሲደረግ በሚገኘው ግኝት መሠረት ክፍተት ከተገኘ ለህግ የሚቀርበው ለህግ ይቀርባል። አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስፈልገው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል። በተለይ ከህዝብ ቀጥታ ጥቆማ ሲገኝ እርምጃዎች ይወሰዳል። የመጣችው ኮታ አነስተኛ ብትሆንም በትክክል ሕዝቡ ጋር እንድትደርስ ጥረት እናደርጋለን። አንዳንዴ ለምልከታ ለ(ሱፐርቪዥን) ከንግድ ቢሮ ጋር ስንወጣም ክፍተቶችን እናገኛለን። ለነዋሪ የተሰጡ ኩፖኖች ፎርጂድ (በሐሰት) ተሰርተው ያገኘንበት አጋጣሚም አሉ። እርምጃ ወስደናል፤ ወደ ፊትም እያጣራን እርምጃ እንወስዳለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጤፍ ገበያ ላይ ሰሞኑን ሰፊ የዋጋ ልዩነት እየታየ ነው። ጤፍን በተመለከተ**

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

**ገበያው እንዲረጋጋ ምን ያህል ሠርታችኋል?**

**አቶ ሙሳቱ፡-** ጤፍን በተመለከተ በስፋት የምንሠራው ከክልሎች ጋር ነው። በከተማዋ ያሉ ሸማች ማህበራት እና ዩኒየኖች ከአምራቾች ጋር ትስስር ፈጥረው በተለይ ምርት በስፋት ከሚመረትበት አካባቢ ጋር ዓመቱን ሙሉ በትስስር እንዲሠሩ እያደረግን ነው። አሁን ደግሞ ፑሽኪን አደባባይ እና ጋርመንት አካባቢ ለበዓል ምርት በሰፊው እንዲገባ እየሠራን ነው። የጋራ ግብረሃይል በማቋቋም የገባውን እህል ለ11ዱም ዩኒየኖች የማከፋፈል ሥራ ተሠርቷል። ዩኒየኑ ለሸማች ማህበራት ሲያቀርቡ፤ ሸማች ማህበራቱ ደግሞ ለህብረተሰቡ ሲያቀርቡ ነበር። ይህ አሁንም በሰፊው እየተሠራበት ነው።

ከበዓል ጋር ተያይዞ ወደ 42 ሺህ 247 ኩንታል እህል ወደ ከተማው ገብቷል። ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ መኮሮኒ እና ፓስታን በዚህ በበዓል ሰሞን ብቻ ወደ ከተማዋ ገብቷል። ይህ የሚቀጥል ነው። ከክልሎች ጋር ከአማራም ሆነ ከኦሮሚያ ክልሎች ጋር ሸማች እና አምራች ዩኒየኖችን በማስተሳሰር ምርት ወደ ከተማ ይገባል። መንግስት በሰጣቸው ተዘዋዋሪ ፈንድ ብር እየከፈሉ እህሉን የሚያመጡ ይሆናል። ይህ ለአንድ ጊዜ ሳይሆን እየቀጠለ የሚሔድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በማህበራት የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ያሉ የጥራት ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ይኖሩ ይሆን።**

**አቶ ሙሳቱ፡-** ምርቶች ከክልል ይመጣሉ፤ ሲባል ዝም ብሎ ጥራት የሌለውን ሰብስቦ ለህብረተብ ማቅረብ ማለት አይደለም። ምርት ሲቀበሉ ቋሚ ውል አለ። በውሉ ውስጥ የጥራት ጉዳይ ተካቷል። በውል ተፈራርመው ምርቱን የሚረከቡ በመሆኑ ምርቱ ላይ የጥራት ችግር ካለ በውሉ መሰረት ተመላሽ ይደረጋል። ይህ ሥራ ላይ ያጋጥማል። ምርቱ ለገበያ ከቀረበ እና ሸማች ከገዛ በኋላም የጥራት ችግር ያጋጥመናል። ይህንን በቋሚ ትስስሩ መሠረት ውሉን ተመርኩዞ ምርቱ እንዲመለስ ይደረጋል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን የጥራት ችግር አያጋጥምም ማለት አይደለም፤ ያጋጥማል፤ ነገር ግን ደግሞ ችግሩ እንዳይፈጠር ወደፊትም በስፋት የሚሠራ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ነዋሪው ሸማች ማህበራትን እንደራሱ ድርጅት በመቁጠር ስመደገፍም ሆነ ስመጠቀም ምን ያህል ዝግጁ ነው?**

**አቶ ሙሳቱ፡-** ለከተማው ነዋሪ የሸማቾች ማህበራት ተደራሽነት መጥፎ የሚባል አይደለም፤ ጥሩ ነው። በ11ዱም ክፍለ-ከተሞች 11 ዩኒየኖች አሉ። መሠረታዊ ሕብረት ሥራ ማህበራት ደግሞ በየወረዳው ይገኛሉ። ስለዚህ ቀረብ ብለው ስላሉ ነዋሪው በደንብ ያውቃቸዋል። አውቆ ከእነርሱ ገዝቶ ከመጠቀም በተጨማሪ የራሴ ናቸው ብሎ ስለሚያምን ሃሳብ እና አስተያየት ይሰጥባቸዋል። በተለያየ መንገድ ጥቆማዎች ይደርሱናል። በተለይ መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ እንዲህ አይነት ተግባር እየተፈፀመ ነው የሚሉ ጥቆማዎች ሲደርሱን የተቋሙ የቁጥጥር (ኢንስፔክሽን) ቡድን ቀጥታ ወደ ቦታው ያመራል። ችግሩን አይቶ እዛው ላይ ውይይት በማድረግ እየተፈታ እንዲሄድ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የእሁድ ገበያ ምን ያህል ለህብረተሰቡ ጥቅም እየሠጠ ነው?**

**አቶ ሙሳቱ፡-** ይህንን ሸማቹ ቢገልፅ መልካም ነው። ምክንያቱም እኛም ስንሸምት እያየን ያለነው እና ያገኘነው ጥቅም ቀላል አይደለም። በተጨማሪ የዳሰሳ ጥናት እናደርጋለን። የጥናት ቡድን መሪ አለ። ቡድኑ የሚሠራው እነዚህ ገበያዎች ለህብረተሰቡ እያስገኙ ያለውን ጥቅም በተመለከተ ነው። በሌላ በኩል በግብይት ዳይሬክቶሬት ሥር የገበያ ጥናት አለ። በየጊዜው ከህዝቡ አስተያየት ይሰበሰባል። ምርቱ ላይ ያለ ዋጋ እና ጥራቱን እያንዳንዱን አይተው ለኤጀንሲው ሃላፊዎች መረጃ ያቀርባሉ። ውይይት ተደርጎበት ውሳኔ እየተሰጠበት ይቀጥላል።

የእሁድ ገበያ መከፈቱ ጥሩ ነው። ህብረተሰቡ ደስተኛ ነው። ነገር ግን በቅርብ ርቀት አይገኙም የሚሉ ሃሳቦች እየተሰነዘሩ ናቸው። ብዛቱን በተመለከተ የሚሰጡ አስተያየቶች አሉ። ነገር ግን ሲጀመር መነሻ የነበሩት አምስት ገበያዎች ብቻ ነበሩ። አሁን ግን አንድ ዓመት ሳይሞላ 124 ቦታዎች ላይ አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል። ይህ አሁንም በቂ አይደለም። ነገር ግን እጅግ በበዛ ቁጥር አብረው መታሰብ ያለባቸው ነገሮች አሉ። ባለሙያ ያስፈልጋል፣ የድንኳን ኪራይ እና ሌሎችም ተጨማሪ ወጪዎች አሉ። ስለዚህ በተቻለ መጠን በተጠኑ ቦታዎች እየጨመርን እንሔዳለን፡፤ ዝም ብሎ ማስፋት

> **“የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራቱ እህል ከገጠር ሲያመጡ ለቀናት የሚያቆዩበት ቦታ የላቸውም። ስለዚህ የከተማ አስተዳደሩ በደንብ ጠንክር አድርጎ መጋዘን መገንባት የሚችሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ማስፈፀም አለበት“**



ከሆነ ግን የምርት ማነስም ሊያጋጥም ይችላል።

ምርት ሳይኖር የማቅረቢያ ቦታ ማስፋቱም ዋጋ የለውም። ሲሰፋ ከአቅርቦቱ ጋር እኩል እንዲራመድ እያደረግን እንሔዳለን። የንግድ መዳረሻን ከ5 ወደ 124 ማሳደጉ በጣም ትልቅ ጉዳይ ነው። በየቦታው ድንኳን ማቆም ሳይሆን በበቂ መጠን ምርት ለማቅረብ እየሠራን ነው። ህዝቡም ገበያዎቹን በሚመለከት እየሰጠ ያለው አስተያየት በአውንታዊ መልኩ መቀበሉን የሚያሳይ ነው። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ዋጋ ጨምረውብናል የሚሉ አቤቱታዎች ይቀርባሉ። አቤቱታዎች ሲቀርቡ ቦታው ድረስ በመሔድ ችግሩን ለመፍታት ጥረት እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- አዎ! አቤቱታዎች አሉ። አንዳንዴ የእሁድ ገበያም ሆነ የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡት ምርት ዋጋ በተለይ የፅዳት መጠበቂያዎች እና የተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶች ነጋዴው ከሚያቀርብበት ዋጋ ብዙ የተለዩ አይደሉም። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሙሳቱ፡-** እውነት ነው፤ ከላይ የጠቀስኩት መዘንጋት የለበትም። አዲስ አበባ ላይ ያሉት ሸማች ማህበራት እንጂ አምራቾች አይደሉም። ወሳኙ ጉዳይ ምርቱ የሚመጣበት ቦታ ላይ ያለው ዋጋ ነው። አርሶ አደሩ ዘንድ ተሰብስቦ የአምራች ህብረት ስራ ማህበሩ ጋር አልፎ ሸማች ማህበሩ ጋር እስከሚደርስ እያንዳንዱ የየራሱ ወጪ አለበት ። ሸማች ህብረት ሥራ ማህበሩ የሚያወጣው ወጪ ታሳቢ ይደረጋል። ሌላው የኢንደስትሪ ምርቱም ላይ አምራቹ የሚያቀርብበት ዋጋ እና ሸማች ጋር እስኪደርስ የሚያስወጣው ወጪ ይሰላል። በተቻለ መጠን ከፋብሪካ እና ከኢንዱስትሪ ባለቤቶች ጋር ብዙ ጊዜ የምንነጋገረው ማለትም በንግዱ በኩል ውይይት ስናካሂድ በምታመርቱበት ዋጋ ለማህበራቱ አቅርቡ እና ለህዝቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ቢደርስ መልካም ነው በሚል ነው። በዚህ መልክ በስፋት እየተሠራ ነው።

አንዳንድ ቦታ ግን ምርቱ ሲጠፋ እና በበቂ ሁኔታ ሳይኖር ሲቀር ካገኙት ጥግ ይገዛሉ፤ ሲገዙ የገዙበት ዋጋ ይወስናቸዋል። ሲሸጡም በገዙበት ዋጋ ላይ ተመስርተው ስለሚሆን ይጨምራል። አርሶ አደሩ ዋጋ ሲጨምር ብቻ፤ ለመጨመር ስለሚገደዱ ይጨምራሉ። ከዚህ ውጪ ዋጋው የሚወሰነው በመነሻነት ምርቱ ሲገዛ፣ ያስወጣው የትራንስፖርት ወጪ እና ሌሎችም የጫኝ እና የአውራጅ የመሳሰሉት ወጪዎች ተደማምረው በሚመጣ ስሌት ብቻ ነው። በመሆኑም ብድግ ብለው ዋጋ አይጨምሩም። የሚይዙት ትርፍ በጣም ትንሽ ነው። ያም ለአስተዳደራዊ ወጪያቸው ብቻ የሚሆን ነው። እንዳይከስሩ ይህንን ማድረግ አለባቸው። ያለበለዚያ ከስረው ያቆማሉ። ስለዚህ ከስረው የመስሪያ ገንዘባቸውን እንዳያጡ የተወሰነ ትርፍ ይዘው ለአባሎቻቸው እና ለነዋሪው በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በእናንተ እይታ በዋናነት ሸማች ማህበራት አካባቢ ያለው ችግር ምንድን ነው?**

**አቶ ሙሳቱ፡-** አንድ ሶስት ችግሮች አሉባቸው። አንደኛው የውስጥ የማኔጅመንት ችግር ነው። ይህንን በጉባኤዎቻቸው እና በቦርዶቻቸው የሚፈቷቸው ናቸው። አንዳንዱ ፈጥኖ ይሔዳል። አንዳንዱ ደግሞ አቅርቦት ላይ እግር መጎተት አለ። እርሱን በሪፎርም እየፈቱት ነው። ሁለተኛው የመስሪያ ቦታ ችግር አለባቸው። የሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራቱ እህል ከገጠር ሲያመጡ ለቀናት የሚያቆዩበት ቦታ የላቸውም። ስለዚህ የከተማ አስተዳደሩ በደንብ ጠንከር አድርጎ መጋዘን መገንባት የሚችሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ማስፈፀም አለበት። በእርግጥ መጋዘን እንዲገነቡ ውሳኔ እንደተላለፈ ደብዳቤው ወደ እኛ ተቋምም ገብቷል። ለእያንዳንዱ ዩኒየን የመጋዘን መስሪያ ተመድቦላቸዋል። ነገር ግን በፍጥነት መሬቱ ተሰጥቷቸው፤ መጋዘኑን ገንብተው ወደ አገልግሎቱ ከመሔድ አኳያ አፈፃፀሙ ሲታይ ከአንዱ ክፍለ ከተማ የሌላው ክፍለ ከተማ ይለያል። አንዳንዱ ፈጥኖ ሰጥቷል፡፤ ለምሳሌ አቃቂ የመገንቢያ ቦታ ሰጥቷል። ሌሎች ግን ገና አልሰጡም።

ሌላው የፋይናንስ ችግር ነው። ይህንን ችግራቸውን ለመፍታት ለእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ 100 ሚሊየን ብር ተዘዋዋሪ ፈንድ ተሰጥቷል። በተጨማሪነት አሁንም የ400 ሚሊየን ብር ውሳኔ ተላልፏል። ይህ የተደረገው የማህበራቱ ካፒታል በጣም ትንሽ በመሆኑ እና በቂ ስላልሆነ በመንግስት እየተደገፉ እንዲያድጉም ጭምር ነው። አጠቃላይ በአንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ብር በመደገፍ እንዲቀጥሉ እየተሠራ ነው። ይህም በቂ ነው ማለት አይደለም፤ ድጋፉ ይቀጥላል። ነገር ግን ማህበራቱ የበለጠ አቅም እየፈጠሩ አሠራራቸውን የማዘመን እና የማስተዳደር አቅማቸው ማደጉ እየታየ ተጨማሪ ፈንድ ይኖራቸዋል። ሌላው ከመንግስት ብቻ ሳይሆን ማህበሩ ህጋዊ ዋስትና ያላቸው በመሆኑ ከማንኛውም አካል ከባንክም ሆነ ከሌሎች ድርጅቶች መበደር እና የፋይናንስ ችግራቸውን ማቃለል ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሙሳቱ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



## የቻድን ድንበር አልፈው የሚገቡ ሱዳናውያን ቁጥር እየጨመረ ነው ተባለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቻድን ድንበር አልፈው የሚገቡ ሱዳናውያን ቁጥር እየጨመረ ነው። ባለፈው ሳምንት ብቻ 20 ሺህ የሚጠጉ ሱዳናውያን ቻድ መግባታቸውን የዓለም የምግብ ፕሮግራም አስታውቋል።

የዓለም ምግብ ፕሮግራም ወደ ቻድ የሚገቡ ሱዳናውያን ቁጥር እየጨመረ እንደሚሄድ ገልፆ፤ በቻድ ከ400 ሺህ በላይ ሱዳናውያን ጦርነትን ሸሽተው በስደተኛ መጠለያ ካምፖች ይገኛሉ ብሏል።

ጦርነቱ ከተጀመረ ወዲህ ከ10 ሺህ እስከ 20 ሺህ የሚጠጉ ሱዳናውያን የቻድን ድንበር አልፈው ገብተዋል ብሏል ድርጅቱ። የጀኔራሎቹ ጦርነት ሊበርድ አለመቻሉ የስደተኞቹን ቁጥር ከፍ እንደሚያደርገው ይጠበቃልም ነው ያለው።

በቻድ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ዳይሬክተሩ ፔር ሆኖራት፥ «የስደተኞች ማዕበል እንደሚኖር እንጠብቃለን፤ በድንበር ላይ የሚገኙ የቻድ ከተሞችም በሱዳናውያን ይሞላሉ» ሲሉ መናገራቸውን ሬውተርስ ዘግቧል።

በሱዳን ከዚህ ቀደም የተነሱ ጦርነቶችን ሸሽት ከ400 ሺህ በላይ ሱዳናውያን የቻድን ድንበር አቋርጠው በ14 የስደተኞች መጠለያዎች ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት በካርቱምና ሌሎች ከተሞች የቀጠለው ጦርነትም ከ100 ሺህ በላይ ሱዳናውያንን ወደ ቻድ ሊያሰድድ እንደሚችል ነው የዓለም ምግብ ፕሮግራም የገለጸው።

አሃዙ ከዚህም ከፍ ሊል ስለሚችል ተገቢው ዝግጅት መደረግ እንዳለበትም አሳስበዋል። በጦርነቱ ምክንያት ቤታቸው የተቃጠለባቸውና ሀብት ንብረታቸውን ያጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያን ሕይወታቸውን ለማትረፍ ስደትን መርጠዋል ያሉት የድርጅቱ ዳይሬክተር፥ በርካታ ሴቶችና ሕፃናትም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል።

ሱዳናውያኑ በቻድ የተጠለሉባቸው አካባቢዎችም በርሃማ ስለሆኑ በፍጥነት የመጠጥ ውሃ እና ምግብ አቅርቦት ለማድረስ ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ ነው ያነሱት። ከሱዳን ጋር ከአንድ ሺህ 400 ኪሎሜትር በላይ ድንበር የምትጋራው ቻድ ጦርነቱ እንደተጀመረ የድንበር መተላለፊያዎቹን ዘግቻለሁ ብትልም በሺዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያን ድንበር አቋርጠው እየገቡ ነው ተብሏል።

## ሩሲያ ከ20 በላይ የጀርመን ዲፕሎማቶችን አባረረች

በጋዜጣው ሪፖርተር




ሩሲያ ከ20 በላይ የጀርመን ዲፕሎማቶችን ከአገሯ ማስወጣቷ ተነገረ። ሞስኮ እርምጃውን የወሰደችው ጀርመን የሩሲያ ዲፕሎማቶች በርሊንን ለቀው እንዲወጡ በማድረጓ ነው።

የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃልአቀባይ ማሪያ ዛካሮቫ የጀርመን ዲፕሎማቶች ከሩሲያ እንዲወጡ ስለመደረጉ ቢገልጹም፥ በርሊን ስለጉዳዩ እስካሁን ማረጋገጫ አልሰጠችም።

የጀርመኑ ቢልድ ጋዜጣ ግን በሞስኮ ከሚገኙ 90 የጀርመን ኤምባሲ ሠራተኞች 34ቱ ከሩሲያ እንዲወጡ ታዘዋል ብሏል። ጀርመን አስቀድማ ከ20 በላይ የሩሲያ ዲፕሎማቶችን ማባረሯ ይታወሳል።

ለዚህም በምክንያትነት ያነሳችው በኤምባሲው የስለላ ሥራ የሚሠሩ ዲፕሎማቶች መበራከት ያሰጋኛል የሚል ነበር ብሏል ሬውተርስ።

የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በበርሊን የተወሰደው እርምጃ የሁለቱን አገራት ግንኙነት ክፉኛ ይጎዳዋል በሚል በመቃወም አጸፋዊ ውሳኔ መተላለፉን ገልጿል።

የሩሲያ ቀዳሚዋ የነዳጅ ገዥ አገር ጀርመን ከዩክሬን ጦርነት መጀመር ወዲህ ከሞስኮ ጋር ግንኙነቷ ሻክሯል።

በርሊን ለኬቭ ሊዮፓርድ ሁለት ታንኮችን ለመስጠት መስማማቷ የቭላድሚር ፑቲንን አገር እጅግ ማስቆጣቱም የሚታወስ ነው።

ታንኮቹን ለዩክሬን መስጠት ከሩሲያ ጋር ጦርነት ውስጥ ያስገባኛል በሚል ሲያቅማሙ የቆዩት መራሄ መንግሥት ኦላፍ ሹልዝ በምዕራባውያኑ ጫና ዘመናዊነታቸው የሚነገርላቸውን ታንኮች ወደ ኬቭ መላካቸው አይዘነጋም።

የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ በርካታ አገራት የሩሲያ ዲፕሎማቶችን ከአገራቸው ማስወጣታቸው ይታወሳል ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በፍ/ባለዕዳ እነ ሳይገን ዲማ ጨርቃጨርቅ ኃ/የተ/የግ/ማ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 219065፣219065፣190489 በ13/12/2012 ዓ.ም በ11/9/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በሰበታ ከተማ ቀበሌ 05 ሳይገን ዲማ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ የሚገኝ የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ማሽኖች የተለያዩ መለዋወጫ ዕቃዎች እና ሁለት ወርክ ሊፍቶች የግል ልማት ድርጅት ያስቀመጠው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 19,592,700 ሆኖ ተጠቃቃሽ መዝገብ ያሉበት ሆኖ ፋብሪካው (ድርጅት) ዓመታዊ ገቢ ግብር ዕዳ 334,866.62 ሳንቲም ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሰኔ 1 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጉድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን።

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት**
**የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

## በድጋሚ የወጣ የግዥ ጨረታ ማስታወቂያ

**የጨረታ ቁጥር ATENO 09/2015**

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር የኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በ2015 ዓ/ም በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውል ሶላር ፓምፕ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ከህጋዊ አቅራቢዎች ለመግዛት እና ለማሰራት እንደሚፈልግ መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ/ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማስታወቂያ ማውጣቱ ይታወሳል፤ ሆኖም ግን በጨረታው ላይ ለውድድሩ የቀረቡት ተወዳዳሪዎችን በማስታወቂያው የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት ስላልተቻለ በድጋሚ ጨረታውን ለማውጣት ተገደናል፤ ስለዚህ በጨረታው ተሳታፊ ለመሆን ለምትፈልጉ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን መሥፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በጨረታው እንድትሳተፉ ተጋብዛችኋል።

- በዘርፉ የታደሰ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡበት፤ መሆናቸውንና በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የምችሉ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው።
- ተጫራቾች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።
- ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር መግለጫ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10(አሥር) ተከታታይ የሥራ ቀናት እና የማይመለስ ብር100/አንድ መቶ /ብር በመክፈል የኦሮሚያ አካባቢ ጥበቃ ባለ ሥልጣን 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 11 ግዥና ንብረት ክፍል መግዛት ይችላሉ።
- የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (CPO) መ/ቤቱ ለውድድር ካቀረበው ጠቅላላ ዋጋ 2% (ሁለት በመቶ) ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
- ተጫራቾች የዕቃዎቹን የዋጋ ዝርዝር በጨረታ ማወዳደሪያ ለወድድር በሚያቀርቡት ሰነድ ላይ ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና አድራሻቸውን በማስፈርና ማህተም በማድረግ፤ የጨረታ መወዳደሪያ ዶክመንቶችን የቴክኒክ እና የፋይናንስ ዶክመንቶችን ኦርጅናሉንና ኮፒውን በተለያየ 4(አራት)ፖስታ በማሸግ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
- ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 11 ኛው ቀን ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በ 8፡30 ሰዓት ላይ ይከፈታል።
- የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ ወይም ከተከፈተ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም።
- ተጫራቾች በጨረታው አሸናፊ ከሆኑ በራሳቸው ትራንስፖርት በማጓጓዝ ፓምፑ የሚቆምበት ቦታ በአካል ሄደው እንስታሌሽን በማድረግ ሥራው ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት መስጠቱ ከተረጋገጠ በኋላ ክፍያው የሚፈጸም መሆኑን እንገልጻለን፤
- የጨረታው አሸናፊ በራሱ ወጪ ዕቃዎቹን መ/ቤቱ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ አለበት።
- መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0118349814 ደውሎ መጠየቅ ይችላሉ።

**አድራሻ፡-** ሳርቤት አደባባይን ዞሮ ወደ ቄራ መሄጃ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስሪያ ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው።

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር የኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን**

# ስፖርት


# መተኪያ ያልተገኘላቸው እንቁዎች

ብርሃን ፈይሳ

የዓለም አትሌቲክስ በቅርቡ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን 40ኛ ዓመት እንደሚያከብር ይታወቃል። ይህንን ተከትሎም ካለፉት ቻምፒዮናዎች እጅግ አስደናቂ የነበሩ ክስተቶችን በመምረጥ አትሌቶችን አወዳድሮ የመሸለም መርሃ ግብር አዘጋጅቷል። በምርጫውም አምስት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተካተዋል፤ እነርሱም ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፣ ገዛኸኝ አበራ፣ ጥሩነሽ ዲባባ እና ሁለት ጊዜ የታጨው ቀነኒሳ በቀለ ናቸው።

የአትሌቶች ሀገር ለሆነችው ኢትዮጵያ በዚህ ምርጫ ውስጥ አትሌቶቿ መካተታቸው አግባብ ቢሆንም፤ ይህ ምርጫ ስፖርቱ እየተጓዘ ያለበትን መንገድ አንዳች ክፍተት መኖሩን የሚጠቁም ነው። እጅግ በርካታ አትሌቶች ያሏት ኢትዮጵያ በተለያዩ ውድድሮች ላይ አሁንም ባንዲራዋን በከፍታ ላይ የሚያውለበልቡላት ጀግኖች አላጣችም። ይሁንና ለምርጫው የቀረቡትን እጩዎች መነሻ በማድረግ በዚህ ወቅት በሀገሪቷ ምርጥ እንጂ እንደ ቀድሞዎቹ ዘመን ተሻጋሪ ተደጋጋሚ ድሎችን ለበርካታ ዓመታት ማስመዝገብ የቻሉ አትሌቶች እንዳልተተኩ አመላካች ሁኔታዎች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል።

ወርቃማው የአትሌቲክስ ትውልድ አካል የሆኑት ብርቅዬ አትሌቶች በሚሳተፉባቸው የዓለም ቻምፒዮናዎች ተፎካካሪ እና አሸናፊ ከመሆን በዘለለ፤ የሚያሳዩት አስደናቂ ብቃት፣ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች አንጻር ለውድድሩ ያላቸው የሞራል ከፍታና ጽናት፣



ተፎካካሪዎቻቸውን ለማለፍ የሚጠቀሙት ብልሃት፣ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ተቋቁመው በድጋሚ የሚቀርቡበት ሁኔታ፣... የስፖርት ቤተሰቡ የትዝታ ማህደር የማይደበዝዝ ነው። የዓለም ህዝብ በምርጫው የተካተቱን አትሌቶች ኢትዮጵያ ከሚለው ስም እኩል ሲያነሳቸው መኖሩም ለዚሁ ነው። አሁን ላይ በዚህ ብቃት የሚገኙ አትሌቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ቁጥራዊ መረጃዎችን መመልከት ብቻውን በቂ ነው። በእርግጥ በሚካፈሉባቸው ውድድሮች ላይ የተመረጡ ወይም የተሻሉ ሆነው የሚገኙ በርካታ አትሌቶች አሉ። ነገር ግን በልዩነት በወጥ አቋማቸው ተለይተው የሚነሱና ድንቅ የሚለው ስያሜም የሚገባቸው አትሌቶች መኖራቸው አጠራጣሪ ይሆናል።

የዓለም አትሌቲክስ በሁለቱም ጾታ ባወጣቸው ዝርዝር መሰረት በምርጫው ውስጥ የገቡት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች እአአ ከ1999 በስፔኗ ሴቪሌ አትሌቲክስ ቻምፒዮና እስከ በርሊን (2009) የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ድረስ የተካፈሉ ብቻ ናቸው። እነዚህ አትሌቶች በወርቃማው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ዘመን የተፈጠሩት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ እና ገዛኸኝ አበራ ድረስ ያሉት ሲሆኑ፤ በእነርሱ እግር ከተተኩት አትሌቶች ደግሞ ቀነኒሳ በቀለ እና ጥሩነሽ ዲባባ ለምርጫ ቀርበዋል። እነርሱን የተኩት አትሌቶችስ ለእጩነት ብቁ ያልሆኑት በምን ምክንያት ሊሆን ይችላል? ከሴቪሌ እስከ በርሊን ስድስት ቻምፒዮናዎች ተካሂደዋል፤ ከዚያ በኋላም ከዴጉ እስከ ኦሪጎን በተመሳሳይ ስድስት ቻምፒዮናዎች ተደርገዋል ታዲያ እንዴት አንድም አትሌት አስደናቂ አቋም አልነበረውም?

ለዚህ ጥያቄ የእጩነት መስፈርትን ጨምሮ በብዙ መንገድ መልስ መስጠት ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን የተሻለ የሚሆነው ክፍተቱ ስለመኖሩ አምኖ ምክንያቱን መመርመር ነው። በእርግጥ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የስፖርት ባለሙያዎች ይህንን ጉዳይ አስቀድመው በማጤን ምክንያቱንና መፍትሄውን ለማመላከት ሞክረዋል። አሁንም ይኸው ሁኔታ እንዳለ በመሆኑ እንደቀድሞው ድንቅ አትሌቶች እየተመናመኑ ያሉት በአቋም መዋዠቅ ወይም ወጥ የሆነ ብቃት ስለሌላቸው እንደሆነ ማንሳት ይቻላል። በዚህ ወቅት በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ሊጠሩ የሚችሉና የተሻሉ ናቸው የሚባሉ አትሌቶች ተሳትፎና ውጤት በመገምገምም ይህንኑ ማረጋገጥ ይቻላል።

ለአብነት ያህል አንጋፋው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ በ6 ዓለም ቻምፒዮናዎች ሲሳተፍ፤ አንድ ጊዜ ብቻ በተደራቢነት 5ሺ ሜትርን ከመሮጡ በቀር በ10ሺ ሜትር ነበር የሚካፈለው። በዚህም 4የወርቅ፣ 1የብር እና 1ነሃስ ሜዳሊያዎችን አስቆጥሯል። የዓለም አትሌቲክስም በዚህ ርቀት ተደጋጋሚ ቻምፒዮና በመሆን ኃይሌን የሚስተካከል አትሌት ባለማግኘቱ እአአ የ1990ዎቹ ድንቅ አትሌት ሲል ሊሰይመው ችሏል።

ድንቅ የተሰኙት እነዚህ አትሌቶች በሚሮጡበት ርቀት የራሳቸው መለያ እስኪመስል በርካታ ጀብዱዎችን ፈጽመው እና ሌሎች ሊያደርጉት ቀርቶ ሊያስቡት የማይቻላቸውን ክብረወሰኖች ሰባብረው ነው። በዚህ ወቅት ያሉ አትሌቶች በአንጻሩ በአንድ ርቀት ጥቂት ሮጠው ወደ ሌላ ስለሚያማትሩ በእነሱ ልክ ሊነሱ አልቻሉም። እንደ አትሌቶች ሀገር ደግሞ ይህ ሁኔታ ያስቆጫል፤ እናም ይህን ምርጫ ጨምሮ በየዓመቱ በሚካሄዱ ምርጥ የዓመቱ አትሌቶች ምርጫ ላይ በእጩነት የሚቀርቡ አትሌቶችን ማጣት በእርግጥም አካሄድን መፈተሽ ተገቢ ስለመሆኑ አመላካች ነው።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የኢፌዴሪ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በ2015 በጀት አመት በጨረታ መጠሪያ ስሙ

1. ብዛታቸው ከ300 በላይ የሆኑ የተለያዩ አይነት ጎማዎች ግዥ
2. የፅዳት እቃዎች(የእጅ ሳሙና) 150 ግራም ብዛት 10,000 ግዥ፤
3. የተለያዩ የደንብ ልብሶች ግዥ
4. የሆቴል አገልግሎት ግዥ በአዲስ አበባ ባለ 5፣ ባለ 4 እና ባለ 3 ኮከብ
5. የባህላዊ ሆቴል አገልግሎት ግዥ በአዲስ አበባ፤
6. የሆቴል አገልግሎት ግዥ በቢሾፍቱ ከተማ ባለ 4 እና ባለ 3 የኮኮብ ደረጃ
7. የሪዞርት አገልግሎት ግዥ በቢሾፍቱ ከተማ፤
8. የሆቴል አገልግሎት ግዥ በአዳማ ከተማ ባለ 4 እና ባለ 3 የኮኮብ ደረጃ
9. የሆቴል አገልግሎት ግዥ በክልል ከተሞች (ባህርዳር፣ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ፣ አርባምንጭ፣ ደሴ እና ጋምቤላ)

የጨረታው ማስረከቢያ ቀነ ገደብ በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ www.ppa.gov.et eGP Portal ላይ የተገለፀ ሲሆን፤ ተጫራቾች ማሟላት የሚጠበቅባቸው ዝርዝር የህጋዊነት ብቃት ማረጋገጫ በሲስተሙ ድረ ገጽ ላይ ይፋ በተደረጉት ዝርዝር የጨረታ ማስታወቂያና የጨረታ ሰነድ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ www.ppa.gov.et በመግባት eGP Portal ላይ መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። በሲስተሙ ያልተመዘገቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎችም ከላይ በተጠቀሰው ድረ-ገጽ ላይ Get Started link (https://egp.ppa.gov.et/egp/home/getting started.የሚለውን በመጠቀም የአንድ ጊዜ የምዝገባ ሂደቱን ማከናወን ይችላሉ።

ጨረታው የሚከፈተው በሲስተሙ በቀጥታ (Online) ሲሆን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ለዚሁ ዓላማ ጥቅም እንዲውል በሰነዱ ላይ የተመለከተውን ሊንክ (Link) በመጠቀም በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መሳተፍ ይችላሉ። የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ተጫራቾች ከሲስተሙ በተጨማሪ መረጃ ሲፈልጉ ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ ማግኘት የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

አድራሻ፡- አራዳ ክፍለ ከተማ፡ ቸርችል ጎዳና፣ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ጀርባ
ግዥ ዳይሬክቶሬት, 3ኛ ፎቅ, የቢሮ ቁጥር - 303
ስልክ ቁጥር- +251 935794508/ 972315211/ 912012703/ 937834350
Email-mitiku.girma@mint.gov.et
የመ.ሣ.ቁ፡- 2490
አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ
ለበለጠ መረጃ በ 9430 ይደውሉ፡፡

**የኢፌዴሪ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር**



## INVITATION FOR BID

**IFB/NO.ECWCT/NCB/PG/123/2015**

1. The Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC) hereby invites registered eligible bidders for supply of Manhole Gate for semera university design and building project.
2. Interested Potential Bidders are required to present renewed relevant Trade License for the Ethiopian fiscal year, VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate and Online Supplier list Registration Certificate together with their offer.
3. Bidding document should be prepared in English language.
4. Interested Potential Bidders obtain a complete set of bidding document from the office of Procurement Department 1 against payment of none refundable fee of Birr 400.00 upon presentation of Trade License renewed for the fiscal year.
5. This invitation of bid is open to all interested potential bidders regardless of their nationality and the bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provision indicated in bidding document.
6. The deadline for bid Submission shall be on May 11, 2023 at 10:00 AM
7. Bid must be accompanied with a Bid Security of an amount of Birr 300,000.00 (Three hundred thousand) in the form of certified cheque (CPO) or Bank guarantee. Bid Bond in the form of insurance bond or in any other form shall not be accepted.
8. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box situated at the office of the Procurement Department, before the closing date and time.
9. Bids will be opened on May 11, 2023 at 10:30 AM in Ethiopian Construction Works Corporation Procurement Department 1 conference room, in the presence of bidders and/or their representatives who choose to attend.
10. The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.
11. Bidders may get further information at the following address:

**Address: Gurd shola behind Athletics Federation Building**
**In front of Andinet International school**
**TelephoneNo. +251-118134527**
**Telegram Channel-ECWC.BID**

**Ethiopian Construction Works Corporation**